
# የብልጽግና ፓርቲ

ፕሮግራም



Addis Star

## ማውጫ


**መግቢያ**

**ክፍል አንድ**

**1. የብልጽግና ፓርቲ አላማና መለያ ዕሴቶች**

1.1 የብልጽግና ፓርቲ ጥቅል አላማ

1.2 መለያ እሴቶቻችን

1.2.1 የህዝቦች ክብር

1.2.2 ፍትሕ

1.2.3 ህብረ-ብሄራዊ አንድነት

**ክፍል ሁለት**

**2 የፖለቲካ ፕሮግራም**

**2.1 የፖለቲካ ፕሮግራማ አላማ:- ጠንካራና ቅቡልነት ያለው ዘላቂ ሀገረ-መንግስት መገንባት**

2.2 የፖለቲካ ፕሮግራም ግቦች

2.2.1 ህብረ-ብሔራዊ አንድነትና ዲሞክራሲ ስርዓት ግንባታን በጽኑ መሰረት ላይ ለመጣል የሚያስችል ብሄራዊ መግባባት መፍጠር

2.2.2 በተቋማዊና ህዝባዊ ባህል ላይ የቆመ አካታች የዲሞክራሲ ስርዓት መገንባት

**ክፍል ሦስት**

**3. የኢኮኖሚ ፕሮግራም**

**3.1 የኢኮኖሚ ፕሮግራም አላማ፡ ልማትና ፍትሃዊ ተጠቃሚነትን የሚያረጋግጥ አካታች የኢኮኖሚ ስርዓት መገንባት**

5.1 የኢኮኖሚ ፕሮግራም ግቦች

5.1.1 የብዝሃ ዘርፍ ኢኮኖሚ መዋቅር መገንባት

5.1.2 ጥራት ያለው የኢኮኖሚ ልማት እና ምርታማነትን መሰረት ያደረገ ማህበራዊ ፍትህ ማረጋገጥ

5.1.3 ሀብት ፈጠራን የሚያሳድግ እውቀት መር ኢኮኖሚ መገንባት

**ክፍል አራት**

**4. ማኅበራዊ ፕሮግራም**

**4.1 የማህበራዊ ፕሮግራም አላማ፡ ሁለንተናዊ ብልጽግናን የሚያረጋግጥ አካታች ማህበራዊ ልማት**

4.2 ጥራት፣ ፍትሐዊነትና አግባብነት ያለው የትምህርት ስርዓት መዘርጋት

4.3 መከላከልን መሰረት ያደረገ የጤና ስርዓት መዘርጋት

4.4 የመኖሪያ ቤታ የማግኘት መብትን የሚያሟላ የቤቶች ልማት

4.5 የሀገራችንን ኢኮኖሚ ያገናዘበ የማኅበራዊ ጥበቃ ሥርዓት

4.6 የሠራተኞችን መብት ማስከበርና የሥራ ሥነ ምግባር ማሳደግ

4.7 የፖለቲካ እና ኢኮኖሚዊ ሴቶችን አካታችነት ማጎልበት

4.8 የወጣቶችን ፖለቲካዊ፣ ኢኮኖሚያዊ እና ማህበራዊ ጠቃሚነት እና ተጠቃሚነት ማስፋት

4.9 ውጤታማና ተጨባጭ የስነ-ህዝብ ሥርዓት መዘርጋት


Addis Standard

4.10 ብዝሀነታችንን ማዕከል ያደረገ የቋንቋ ፖሊሲ

4.11 ሀገራዊ ክብርን እና ሀገራዊ መቀራረብን የሚያመጣ የስፓርት ልማት

4.13 የተፈጥሮና ሰው ሰራሽ ሀብቶችን ዘመንን እንዲሻገሩ የሚደርግ ጥበቃ

**ክፍል አምስት**

**5. የውጭ ግንኙነት ፕሮግራም**

5.1 የውጭ ግንኙነት ዋና አላማ፡ ሀገራዊ ክብርን ማዕከል ያደረገ የውጭ ግንኙነት

5.2 የውጭ ግንኙነት ግቦች

5.2.2 ለትብብርና ለጋራ ተጠቃሚነት ትኩረት በመስጠት አጋሮቻችንን ማስፋት

5.2.4 ለጎረቤት ሀገራት ትኩረት በመስጠት ዘርፈ ብዙ የጋራ ተጠቃሚነትን ማረጋገጥ

5.2.5 የኢትዮጵያውያንና ትውልደ-ኢትዮጵያውያን ተሳትፎ ማሳደግ

Addis Standard

**መግቢያ**

I. ሀገራችን ኢትዮጵያ በኢህአዴግ አመራር  በማህበራዊ፣ በኢኮኖሚያዊ እና በፖለቲካዊ መስኮች በርካታ አዎንታዊ ለውጦችን አስመዝግባለች። እነዚህን ማህበራዊ፣ኢኮኖሚያዊ እና ፖለቲካዊ  ለውጦች አስጠብቆ ማስፋት፣ ስህተቶችን ማረም እና የመጪውን ትውልድ ጥቅምና ፍላጎት በዘላቂነት ለማሟላት  የድርጅታችን ኢህአዴግ ቅርጽና ይዘት ወቅቱ ለሚጠይቀው ትግል በሚመጥን መልኩ መቀየር አለበት። በኢኮኖሚው መስክ ሀገራችን በኢህአዴግ አመራር  ለተከታታይ ዓመታት ባለ ሁለት አሃዝ ኢኮኖሚያዊ እድገት፣ የድህነት ቅንሳ፣ የመሰረተ ልማትና ማህበራዊ አገልግሎት መስፋፋት ግለቱን ጠብቆ ማሰቀጠል ያስፈልጋል። በፖለቲካው መስክ የብሄር፣ ብሄረሰቦችና ህዝቦች እኩልነትን ያረጋገጥ ህገ መንግስታዊ ፌደራላዊ ስርዓት መዘርጋቱን አጠናክሮ መሄድን ይጠይቃል።  በውጭ ግንኙነት መስክ ሀገራችንን በዓለም አቀፍ መድረክ የፍትህና የገለልተኝነት ተምሳሌት መሆኗን አስጠብቆ መዝለቅ ይጠበቅብናል።

II. አሁን ሀገራችን በደረሰችበት እድገት ደረጃ ከዚህ በፊት በተከተልነው የልማት ፋይናንስ ሞዴል  በኢኮኖሚና ማህበራዊ መስክ ያሰመዘገብነውን እድገትና ልማት በተመሳሳይ መንገድ አስጠብቆ ማስቀጠል ከባድ ፈተና የሆነበት ደረጃ ላይ ደርሰናል። በመሆኑንም እድገቱን አንድም  አማራጭ የእድገት ምንጭ በመቀየስ፣ በሌላ በኩል ደግሞ በመንግስት ጉድለት ምክንያት የሚፈጠረውን የሀገር ሃብት ብክነትና ዝርፊያ በመከላከል የሀገራችንን ህዝቦች ፍትሃዊ ተጠቃሚነት ማረጋገጥ ያስፈልጋል። በፖለቲካው መስክ ዐቢይ ማጠንጠኛ የሆነው የብሄር ማንነትን እና ሀገራዊ ማንነትን አጣጥሞ በዘላቂነት የሚያስኬድ የሀገርና ዲሞክራሲያዊ ስርዓት ግንባታ ማካሄድ ያስፈልጋል። ህብረተሰብን በጎራ ከፍሎ የመንግስት ፖሊሲዎች ለውስን ማህበራዊ ቡድን ያጋደሉ እንዲሆኑ የሚያደርገው  የመደብ ትንተና መስፋትና አካታች ሊደረግ ይገባል። የዴሞክራሲ ስርዓት ግንባታ እንቅፋት የሆነውና በእኔ አውቃለሁ መንፈስ የሚቃኘው ኢኮኖሚያዊ ፍላጎቶች ከዴሞክራሲያዊ ጥያቄዎች የላቁ ናቸው የሚለው ምሉዕነት የሌለው  ትንተና የፖለቲካ ፕሮግራም ሀገራዊ ሁለንተናዊ ብልጽግናን በሚያስቀድሙ የፖለቲካ እይታዎች መተካት ይኖርበታል። የሀሳብና የተግባር ተቃርኖ የሞላው ኢ-ዴሞክራሲያዊና አፋኝ ስርዓት እንዲዘረጋ ያደረገው የውስጠ ድርጅት ዴሞክራሲ መቀጨጭ  ተገርስሶ ግልጽና ለሁሉም የሀገራችን ህዝቦች የተዘረጋ የዴሞክራሲ ስርዓት እንዲኖር ማድረግ ነባራዊው ሀገራዊ ሁኔታ ግድ የሚለው ጉዳይ ነው።  በድምሩ ሀገራችን በኢህአዴግ አመራር በቆየችባቸው ዓመታት የነበሩ ፖለቲካዊ፣ ኢኮኖሚያዊ፣ ማህበራዊ  እና የዲፕሎማሲ ጉድለቶችን ነቅሶ በማውጣት ያለማወላወል እንዲታረሙ ማድርግ ያስፈልጋል። ድርጅታችን ኢህአዴግ በትጥቅ ትግል ለድል ከበቃ በኋላ ለ28 ዓመታት ሀገርን በመራበት ታሪኩ የተንቀሳቀሰበት ሀገራዊና ዓለማቀፋዊ ፖለቲካዊ አውድ በመሰረቱ የተለወጠ ሆኗል። አሁን ላይ እንደፓርቲ የፖለቲካ ቋሚ ማንነት የተከተልናቸው የርዕዮት-ዓለም እሳቤዎች ፖለቲካዊ አዋጭነታቸው መንምኗል።

Addis Standard

ፓርቲያችን ከዘመናዊ የፖለቲካ ጨዋታ ህግጋት ጋር ተናቦ የሚሄድ የእይታ ለውጥ በአጭር ግዜ በማካሄድ እየተለወጠ ካለው ምህዳር ጋር መዋጀት ካልቻለ እንደድርጅት ብቻ ሳይሆን እንደሀገርም ከፍተኛ ጥፋትን ሊያስከትል የሚችል የቆሞ ቀርነት አዙሪት ውስጥ ልንዘፈቅ እንደምንችል በሀገራዊ ለውጡ ዋዜማ ያሳለፍነው ሀገራዊ ሁኔታ ፍንትው አድርጎ ያሳየው እውነታ ነው። የንቅዘት ምንጭ የሆኑ ተቸካይ እሳቤዎችን አስወግዶ ጊዜውን ባገናዘበ እሳቤ መቀየር በይደር የማይታለፍ አንግብጋቢው ድርጅታዊ ጉዳይ እንደሆነ መረዳት ያስፈልጋል።

III. ሀገራችን ኢትዮጵያ ሀገር ተረካቢ መጪውን ትውልድ ጥቅምና ፍላጎት የሚያስከብር አስተማማኝ መሰረት ዛሬ ላይ በመገንባታ ሰላም፣ ዲሞክራሲ፣ ህብረ ብሄራዊ አንድነት፣ የዜጎች ክብር፣ ፍትህ እና  የጋራ ብልጽግና የተረጋገጠባት ሀገር መገንባት ይኖርባታል። ሆኖም ግን በቀድሞ ኢህአዴግ ቅርጽና ይዘት እነዚህን ድሎች ጠብቆ ማስፋት፣ስህተቶችን ማረም እና የመጭውን ትውልድ ጥቅም የማስከበር አላማዎችን በተሟላ መልኩ ማሳካት አይቻልም። በመሆኑም አካታች የፖለቲካና ኢኮኖሚ ስርዓት የሚገነባ የብልጽግና ፓርቲ  የሚሰኝ የኢህዴግ አባል ድርጅቶችን እና አጋር በሚል ሲጠሩ የነበሩ የፖለቲካ ድርጅቶች በማካተት ህብረ ብሄራዊ ፓርቲ ማቋቋም አስፈልጓል።

IV. ፓርቲያችን ከግንባርነት ወደ የአላማ ወጥነት ወዳለው ህብረ ብሄራዊ ፓርቲነት  የሚያደርግው ጉዞ ሰፊ የሀገራችንን ህዝብ የሚያቅፉ ነገር ግን በእይታ ግድፈት ከሀገራዊ ፖለቲካዊ ውሳኔ የተገለሉ የኢህአዴግ አጋር ፓርቲዎች በእኩልነት የሚሳተፉበት ድርጅታዊ አወቃቀርን ማምጣት ያስችላል። በሌላ በኩል ህብረ ብሄራዊ ፓርቲው  የውክልና ፖለቲካን ህዳጣንን አካታችንና አሳታፊ በሆነ መልኩ እንዲሰፍን ያደርጋል። በእህት ድርጅቶች መካከል እየተፈጠሩ ያሉ አላስፈላጊ መጓተቶችንም ያስቀራል። በዚህም መሰረት የውክልና እና ብቃትን መሰረት ያደረገ ውሳኔ አሰጣጥ ትስስሮሽን በማጠናከር በሃሳብ ልዕልና ላይ የተመሰረተ ዘመናዊ የፖለቲካ ፉክክርና ትብብር መሰረት እንዲይዝ  የሚያስችልም ነው። ይህም ጠንካራ የመድበለ ፓርቲ ፖለቲካ እንዲኖር በማድረግ በፖለቲካ ኃይሎች መካከል ጤናማ ፉክክርና ትብብር እንዲያብብ በማድረግ ሀገራችን የተያያዘችው ዴሞክራሲያዊ የለውጥ ሂደት ቀጣይነት ኖሮት እንዲጠናከር የሚያግዝ መሆኑን እናምናለን።

V. የኢህአዴግ እህት ድርጅቶችና አጋር ድርጅቶች ሀገርን ባስተዳድርንበት ባለፉት ዓመታት በአመዛኙ ተመሳሳይ የፖለቲካ ዓላማ፣ ፕሮግራም እና መሰረታዊ አቅጣጫ ይዘን በመሆኑ ጠንካራ ጎኖችን በማስቀጠል እና ስህተቶችን በማረም ወደ ሚቀጥለው የትግል ምዕራፍ ለመሸጋገር አስቻይ አቅም አለን። በመሆኑም ይህ የጋራ ትግል ታሪክና የአላማ አንድነት ህብረ ብሄራዊ ውህድ ፓርቲ ለሆነው ብልጽግና ፓርቲ ስኬታማነት ከፍተኛ አስተዋጾ አለው። እንደድርጅት በወሳኝ ሀገራዊ ፖለቲካዊ አጀንዳዎች ዙሪያ ግንባር በመፍጠር ቢያንስ ላለፉት ሶስት አስርት አመታት ታግለናል። የመንግስት ስልጣን በመጨበጥ የጋራ የፖለቲካ ፕሮግራሞቻችንን ተግብረን ተጨባጭ ሀገራዊ እድገትን ማስመዝገብ ችለናል። የምናካሂደው ውህደት እያንዳንዱ የእህት ድርጅት የነበረውን የአላማና የተግባር ውህደት በአዲስ መንፈስ ይበልጥ በማጠናከር የተሻለ ኃይል

Addis Standard

እንድናሰባስብ በማድረግ በቀጣይ ለላቀ የአላማ አንድነትና ሀገራዊ ድል የሚያበቃ መልካም አጋጣሚን የሚፈጥር ይሆናል።

## ክፍል አንድ

### 1. የብልጽግና ፓርቲ አላማና መለያ ዕሴቶች

ፓርቲያችን ሀገራችንን የሚመለከትበት የዕይታ ማዕቀፍ በጥቅሉ የነበረውን ጠንካራ መሰረት በማስጠበቅ እና ውስንነቶችን በማረም ሁለንተናዊ የብልፅግና ምዕራፍ መክፈት የሚል ነው። በመሆኑም በተለያዩ ቡድኖች፣ መደቦች፣ ማንነቶች ወዘተ የሚስተዋሉ ዋልታ ረገጥ አስተሳሰቦች ሚዛን ጠብቀው እንዲሄዱ ያደርጋል። በዚህም ምክንያት ከወግ አጥባቂ ዝንባሌዎችም ሆነ አፍርሰው ከሚገነቡ አስተሳሰቦች ይልቅ ህዝቡን የሚጠቅሙ መካከለኛውን መንገድ ተመራጭ ያደርጋል። በሀገራችን የቀኝ እና የግራ አሠላለፍ ልማድ በመሠረቱ ከመደባዊ ውግንናና ዝንባሌ ባሻገር አጠቃላይ ሀገረ-መንግስቱ ዙሪያ ባሉ ዕይታዎች ላይ የሚያጠንጥን መሆኑን በመረዳት እነዚህን አመለካከቶች የሚያቀራርብ አሠላለፍን ይከተላል። ይህ አተያይ ነገሮችን ቋሚ አድርጎ ከመመልከት ይልቅ ነባራዊ እውነታን እያነበበ፣ መርህን ተከትሎ ጉዞን የመፈተሽ እና በጥናት ላይ እየተመሠረተ የሚቀጥል መርህ ተኮር ፕራግማቲክ እሳቤን ይከተላል። በዚህም ምክንያት ሁሉንም ኢትዮጵያውያን የሚያሰባስብና የፓርቲው ማኅበራዊ መሠረት ማድረግ የሚያስችል አካታች ፖለቲካዊ ጉዞን ተመራጭ ያደርጋል። ፓርቲያችን ሀገራችን ለሁላችንም ትበቃለች የሚል ጽኑ ሃሳብ በመያዝና የዕጦት አስተሳሰብን በመሻገር ለሁሉም ዜጎች የምትሆንና ሁሉም በኩራትና በምቾት የሚኖርባት የበለጸገች ኢትዮጵያን ለመፍጠር ትግል ያደርጋል። ይህንን ዓላማ የሚጻረሩ በግራም ሆኑ በቀኝ የተሰለፉ አፍራሽ አስተሳሰቦችንና ተግባሮችን ሁሉ ፓርቲያችን በጽኑ ይታገላል።

### 1.1 የብልጽግና ፓርቲ ጥቅል አላማ

የፓርቲያችን ጥቅል አላማ "የበለጸገች ኢትዮጵያን እውን ማድረግ ነው"። ብልጽግና ስንል ፈርጀ ብዙ ትርጓሜን አዝሎ የኢኮኖሚ፣ ፖለቲካ እና ማህበራዊ ገጽታ ያለው ነው። የኢኮኖሚ ብልጽግና፣ የህዝቦች መሰረታዊ ፍላጎቶች በተገቢና በዘላቂነት ለማሟላት ፈጣን እና ሁለንተናዊ ዕድገት በማስመዝገብና ዓለም አቀፍ ተወዳዳሪነት ያለው ኢኮኖሚ በመገንባት ፍትሃዊ ተጠቃሚነትን ማረጋገጥ፣ የህዝቦችን ድህነት፣ እርዛት እና ኋላቀርነት ቀርፎ ሁሉን አቀፍ ብልጽግና በሃገራችን እውን ሆኖ ማየት ነው። የፖለቲካ ብልጽግና ስንል ለዴሞክራሲ ባህል ማበብ አስፈላጊ የሆኑ ባህልና ተቋማት በመገንባት፣ የህዝቦች ነፃነትና እኩልነት ተረጋግጦ፣ ሁሉም ኢትዮጵያውያን ሰብአዊ እና ዴሞክራሲያዊ መብቶቻቸው ተከብረውላቸው፣ ህብረ ብሄራዊ አንድነቷ የተረጋገጠባት ፌዴራላዊት ዴሞክራሲያዊት ኢትዮጵያ በፅኑ መሰረት ላይ ማቆም ማለታችን ነው። ማህበራዊ ብልጽግና መልካም ሀገራዊ ወጎች፣ እሴቶችንና ባህሎችን በማዳበር በስነ ምግባር የታነፀ ትውልድ ማፍራት፣ ለኑሮ ምቹ የሆኑ አከባቢዎች መፍጠር፣ የማህበረሰባችን

Addis Standard

ጤና ተጠብቆ፣ ጥራት ያለው ትምህርት ለሁሉም ተዳርሶ ማየት እና በህዝቦች መካከል አዎንታዊ ሰላም በመፍጠር ሁለንተናዊ ብልጽግናን ማረጋገጥ ማለት ነው።

### 1.2 መለያ እሴቶቻችን

ዕሴቶቻችን ቅድሚያ ዋጋ የምንሰጣቸውና የምንታገልላቸው ወደ ብልጽግና ዓላማ መድረሻ መንገዳችን አመልካቾች ናቸው። በምንጓዝበት መንገድ ሁሉ በሚገጥሙን የተለያዩ አጣብቂኞች ሁሉ ቅድሚያ የምንሰጠው ለእነዚህ ዕሴቶቻችን ይሆናል።

#### 1.2.1 የህዝቦች ክብር

የህዝቦች ክብር ስንል ኢትዮጵያውያን ሀገራቸው ልታስጠብቅላቸው የሚገቡ ሰብዓዊ ክብርን እና በሀገራቸው ለመመካት የሚያስችላቸውን ሁኔታ መፍጠርን ይመለከታል። የህዝቦች ክብር የግለሰብ ነጻነት፣ የቡድኖች እኩልነት እና የሀገር ሉዓላዊንት አመላካትን አቅፎ በግለሰብ፣ በማህበረሰብ እና በሀገር ደረጃ የሚታይ ነው። ማህበረሰባዊና ሃገራዊ ክብር ህዝቦች በአገራቸውም ሆነ በዓለም መድረክ ቀና ብለው መሄድ መቻል ነው። ይህ የብዙ ነገሮች ድምር ውጤት ነው። በዋነኝነት የሃገራዊ ልማት፣ የአካል እና የንብረት ፍትህና ብልጽግና ጥያቄዎችን በመመለስ ህዝቦች በሀገራቸውና በማህበረሰባቸው ክብር እንዲሰማቸው ማድረግ ያስፈልጋል። በተመሳሳይም ደግሞ በዓለም መድረክ ስሟ በበጎ የሚነሳ ሀገር በመገንባት የህዝባችንን ክብር ከፍ ማድረግ ያስፈልጋል። በዜግነት ክብር የሀገራችንን ስም ከፍ ማድረግ፤ ከፍ ያለች ሀገር በመገንባት ደግሞ የዜግነትን ክብር ወደ ላቀ ደረጃ ማድረስ ተመጋጋቢነት ያላቸው ጉዳዮች ናቸው። የብልጽግና ፓርቲ አላማ ይህንን ከላይ የተገለፀውን እውነታ በመገንዘብ የህብረተሰቡን ሰብዓዊ ክብር ለማስጠበቅ ይሰራል። ሰው ክቡር ነው። ሰው ሰው በመሆኑ ብቻ ሊከበር ይገባል። ሃይማኖቱ፣ ዘሩ፣ ብሄሩ ወይም ፆታው ብሎም ሀብቱና ድህነቱ ከግምት ሳይገባ መሰረታዊ ነፃነቱ ሊከበርለትና፣ በዕኩል አይን ሊታይ፣ ፍትህን ሊያገኝ ይገባል ብለን እናምናለን። የዜጎችን ሰብዓዊ ክብር ማስጠበቅ ፓርቲያችን የሚቆምለት አላማ ነው። ሀገራችን የህግ የበላይነትን በማስፈን፣ ዘላቂ የፍትህ ስርዓት በመገንባት፣ መሰረታዊ ሰብዓዊ መብቶችን በማክበር፣ የማህበረሰባችንን ሰላምና ደህንነት በመጠበቅ፣ ሰዎችን የሚያስቀድም የኢኮኖሚ ዕድገትን በማሳለጥና ሁሉን አቀፍ ብልፅግናን በማምጣት ሰብዓዊ፣ማህበረሰባዊ እና ሀገራዊ ክብርን ማስጠበቅ ከእሴታችን አንዱ ነው።

#### 1.2.2 ፍትሕ

ፍትህ እሴታችን ነው ስንል፣ በሀገራችን ማንኛውም ቡድን ወይም ግለሰብ ከሌሎች የተለየ ተጠቃሚ አሊያ ተጎጂ እንዳይሆን መስራት ማለታችን ነው። በመሆኑም ፍትህ ፖለቲካዊ፣ ኢኮኖሚያዊ እና ማህበራዊ ገጽታ የተላበሰ ነው። ኢትዮጵያውያንን በእኩል አይን የሚያይና የሚዳኝ፣ ሁሉም ኢትዮጵያዊ በህግ ፊትና በሃገራችን እኩል የሚታዩበትና በፍትሃዊ መልኩ ተጠቃሚ የሚሆኑበት፣ የብዙሃን ሆነ የህዳጣን መብትና ነጻነት የሚከበርበት፣ ሰው በሰውነቱ በእኩል የሚታይበት፣ ከበደልና ጭቆና ነጻ የሚሆንበት፣ የማሰብና ህሳብን በነጻነት የመግለጽ መብት የሚከበርብት፣በዋና ዋና የሀገሪቱ ጉዳዮች ሁሉም ዜጋ ውሳኔ ላይ ተሳታፊ የሚሆንበት እንዲሁም የሀብት፣ የስልጣንና

Addis Standard

የመብት ክፍፍሉ ርዕታዊና አግባብ፣ ለህሊና የማይቆረቁር የሆነበት ማህበራዊ ፍትህ የሚያሰፍን የፖለቲካዊ ኢኮኖሚ ስርዓት ለመፍጠር ፓርቲያችን ይሰራል።

### 1.2.3 ህብረ-ብሄራዊ አንድነት

የፓርቲያችን ዋነኛ ዓላማ ህብረ-ብሄራዊነቱ የተጠበቀ አንድ የፖለቲካና የኢኮኖሚ ማኅበረሰብ መገንባት ነው። ህብረ-ብሄራዊ ስንል የብሔር፣ የኃይማኖት ወይም ሌላ ማንነቶችን ያቀፈና ማንንም ያላገለለ ማኅበረሰብ ማለታችን ነው። የፓርቲያችን ህብረ-ብሄራዊነት በሁሉ-አቀፍነት፣ በብዝሃ-ልሳንነት እና በአሳታፊነት ሊገለጽ ይገባል ብሎ ፓርቲያችን ያምናል። ህብረ ብሄራዊ አንድነት ብዝሃነትን እንደጸጋ የሚመለከት ለሁሉም ብሔር፣ ብሔረሰቦችና ህዝቦች እውቅና የሚሰጥና ካላቸው የታሪክ ትስስር፣ተመሳሳይ አሁናዊ ሁኔታ፣ የጋራ ጥቅም እና ተስፋ በመነሳት ጠንካራ ህብረትና ትብብር ሊኖራቸው ይገባል የሚል እሴት ነው። ህብረ-ብሔራዊ አንድነት ማንነታችን እርስ በርሱ የተጋመደ፣ የተሰናሰለ እና የተዋሃድ መሆኑን አመላካች ነው። ሕብረ ብሔራዊ አንድነት ለጋራ አላማና ግብ አብረን መቆም፣ አብረን መስራት እንዳለብን፣ ዕጣ ፈንታችን እጅጉን የተቆራኘ መሆኑን በመገንዘብ መደጋገፍ፣ መተጋገዝ እንደሚገባን የሚያስገነዝብ አመለካከት ነው። ሕብረ ብሔራዊ አንድነት ታሪካዊና ነባራዊ በደሎችን የማያድበሰብስ ነገር ግን መስተካከልና መታረም ያለባቸውን የተዛቡ፣ ኢ-ፍትሃዊ ግኙኝነቶች በማረም ህብረትና ወዳጅነትን የሚያጠናክር አካሄድ ነው። ሕብረ ብሔራዊ አንድነት ልዩነቶችን፣ የሚከፋፍሉ እና የሚያጣሉ ሁኔታዎችን ከማጉላት ይልቅ የሚያቀራርቡና የሚያስተሳስሩንን እውነታዎች በማጉላት፣ ከትናንትና ይልቅ ዛሬና ነገ ላይ በማተኮር እህትማዊ/ወንድማዊ ሕብረትን በብሔሮች መሃከል ማጠናከርን ይመርጣል። ህብረ-ብሔራዊ አንድነት ብዙ ሆነን አንድ፣ አንድ ሆነነም ብዙ የምንሆንበት፣ ለጋራ ግብና አላማ የምንደመርበት ቀመር ነው። በብዝሃነታችን ደምቀን፣ በአንድነታችን በርትተን ወደፊት የምንራመድበት የውበትና የጥንካሬያችን ምንጭ ነው። በጥቅሉ ፍትህ ከሰፈነ፣ ሰብዓዊ ክብር ከጎለበተና ብልፅግና ከመጣ እንደ ሀገር የመቀጠል ተስፋችን ይለመልማል። ሆኖም ግን ህብረ ብሄራዊ አብሮነት እነዚህ ምሰሶዎች ከተሳኩ በኋላ የሚመጣ ብቻ ሳይሆን ለአላማዎች ስኬትም አይነተኛ ድርሻ የሚወጣ አስቻይ አቅም በመሆኑ ፓርቲያችን በህብረት ሆነን እንበለጽጋለን፤ በልጽገንም በህብረት እንኖራለን በሚል መርህ ህብረ ብሄራዊ አንድነት ማረጋገጥ በከፍተኛ ትኩረት የሚሰራበት እሴት ይሆናል።

Addis Standard

## ክፍል ሁለት

# 2 የፖለቲካ ፕሮግራም

## 2.1 የፖለቲካ ፕሮግራማ አላማ:- ጠንካራና ቅቡልነት ያለው ዘላቂ ሀገረ-መንግስት መገንባት

የብልጽግና ፓርቲ የፖለቲካ ፕሮግራም ዋነኛ አላማ ጠንካራና ቅቡልነት ያለው ሀገረ-መንግስት መገንባት ነው። ከጠንካራ ሀገረ መንግስት ግንባታ አንጻር የብልጽግና ፓርቲ ሀገረ-መንግስት ህዝብን ከቀጥተኛ የህልውና አደጋ ተጠብቆ የልማት፣ የእኩልነት እና የነጻነት ህዝባዊ ፍላጎቶችን ለሟሙላት የሚያስችል ነጻ፣ ገለልተኛና ብቃትን መሰረት ያደረገ ሀገራዊ ተቋማዊ አደረጃጀት መገንባት ያስፈልጋል ብሎ ያምናል። በመሆኑም ሀገረ-መንግስት ግንባታ ውጥናችን ተቋማዊ መሠረት ያለው እንዲሆን የብልጽግና ፓርቲ ግቡ አድርጎ ይንቀሳቀሳል። ከሀገረ መንግስት ቅቡልነት አንጻር የብልጽግና ፓርቲ ለኢትዮጵያ ሀገረ-መንግስት ጥንካሬ በተደጋጋሚ ፈተና የሚሆነው በሕገ-መንግስታችን የተቀመጠውን አንድ የፖለቲካና የኢኮኖሚ ማኅበረሰብ የመፍጠር ግብ ማሳካት አለመቻላችን ነው ብሎ ያምናል። በመሆኑም የሀገረ-መንግስቱን ቅቡልነት የሚጨምሩና ብሔራዊ መግባባትን የሚያመጡ፣ የሕዝቦችን ግንኙነት በሚያሳልጡ እና የዕርቅ መንፈስን በሚያጎለብቱ ፖለቲካዊ እርምጃዎች ላይ ትኩረት አድርጎ ይንቀሳቀሳል። ፓርቲያችን የሀገረ-መንግስት ግንባታችን ሕብረ-ማንነታዊነት የተላበሰና ብዝሃነትን የሚያንጸባርቅ መሆን እንዳለበት በጽኑ ያምናል።

### 2.2 የፖለቲካ ፕሮግራም ግቦች

#### 2.2.1 ህብረ-ብሔራዊ አንድነትና ዲሞክራሲ ስርዓት ግንባታን በጽኑ መሰረት ላይ ለመጣል የሚያስችል ብሄራዊ መግባባት መፍጠር

2.2.1.1 የብልጽግና ፓርቲ የቆመላቸው የፖለቲካ አላማዎች እንዲሳኩ ፓርቲው ትኩረት ሰጥቶ ከሚሰራባቸው ነገሮች አንዱ የብሄራዊ መግባባት ጉዳይ ነው። ህብረ-ብሔራዊ አንድነታችንን ለማጠናከር፣ ለዲሞክራሲ ስርዓቱም ምቹ መደላድል እንደሚኖር ለማረጋገጥ፣ የሀገረ-መንግስቱን ቅቡልነትም ከፍ ለማድረግ የብልጽግና ፓርቲ ብሔራዊ መግባባትን ለማዳበር በፅኑ ይሰራል።

2.2.1.2 የብልጽግና ፓርቲ በሀገሪቱ የፓለቲካ ልሂቃን መካከል የሚታየው ዋልታ ረገጥነት እና እጅግ መሰረታዊ በሆኑ ጉዳዮች ሳይቀር ያለው የከረረ ቅራኔ እና አለመተማመን ጤናማ እንዳልሆነ ይገነዘባል። ፓርቲው የሀሳብ ልዩነቶች፣ የጥቅምና የፍላጎት አለመጣጣሞች ተፈጥሯዊ መሆናቸውን ይረዳል። እንደዚህ ያሉ ልዩነቶች አይቀሬና በዲሞክራሲ አግባብ ሊስተናገዱ ቢችሉ ጠቃሚና ገንቢ ናቸው ብሎም ያምናል።

Addis Standard

ነገር ግን ሀገራዊ ህልውናን እና ህብረ-ብሄራዊ አንድነታችንን አጠያያቂ የሚያደርጉ፣ የአገረ-መንግስቱን ቅቡልና የሚሸረሽሩ የከረሩ አለመግባባቶች ግን አሉታዊ ተጽኖአቸው ከፍ ያለ እንደሆነ ይገነዘባል። በመሆኑም የብልጽግና ፓርቲ እጅግ መሰረታዊ በሆኑ እና ለሀገረ መንግስቱ ቅቡልነት ወሳኝ በሆኑ ጉዳዮች ላይ ሰፊና ጠንካራ ብሄራዊ መግባባት እንዲዳብር ይሰራል።

2.2.1.3 ፓርቲያችን ብሄራዊ መግባባትን ለማዳበር በሚያደርገው እንቅስቃሴ ቅድሚያ ሰጥቶ ከሚሰራቸው ተግባራት አንዱ በሀገራችን የቂምና የጥላቻ ታሪክ ምዕራፍ እንዲዘጋ ማድረግ ነው። ይህን ለማሳካት ባህላዊና ዘመናዊ የእርቀ ሰላም ግንባታ አማራጮችን በመጠቀም እርቀ ሰላምን ለማምጣት በቁርጠኝነት ይታገላል። ለቀጣዩ ትውልድ ቂምና ቁርሾ ሳይሆን ሰላምና ወንድማማችነትን ለማውረስ የእርቀ ሰላም አማራጮችን ሁሉ አሟጦ ይጠቀማል።

2.2.1.4 የሀሳብ ልዩነቶች ለማጥበብ እና ቅራኔዎችን ለማስወገድ ፓርቲያችን በጥናት ላይ የተመሰረተ ውይይትን ወይም ተዋስዖን የሚያስቀድሙ ድርድሮችን በተከታታይና በቀጣይነት እንዲካሄዱ በማድረግ የብሄራዊ መግባባትን ለማዳበር ይሰራል።

2.2.1.5 የብልጽግና ፓርቲ በአገራችን የምንፈጥረው የፖለቲካና የኢኮኖሚ ማኅበረሰብ ህብረ ብሄራዊ አንድነትን የጠበቀና የሁሉም ማንነቶች ነጸብራቅ የሆነ የብሔር፣ ብሔረሰቦችና ህዝቦች ባህልና ማንነት የጠበቀ መሆን እንዳለበት በጽኑ ያምናል። ስለሆነም የምንገነባው ማኅበረሠብ ህብረ-ብሔራዊና በአጠቃላይም ህብረ-ማንነታዊ እንዲሆን፣ ዜጎችም ብዝሃነትን የተረዱና የሚያከብሩ እንዲሆኑ አበክሮ ይሠራል።

### 2.2.2 በተቋማዊና ህዝባዊ ባህል ላይ የቆመ አካታች የዲሞክራሲ ስርዓት መገንባት

2.2.2.1 የብልፅግና ፓርቲ የበለፀገችና ህብረ ብሔራዊ አንድነቷ የተረጋገጠ ኢትዮጵያን ያለ ዴሞክራሲ እውን ማድረግ አይቻልም ብሎ ያምናል። የህዝቦች ድምር የልማት፣እኩልነትና ነጻነት ፍላጎት የሚያሟላ ሁለገብ የሆነ ብልፅግና እንዲመጣ የዴሞክራሲ አጀንዳ አንገብጋቢ ጉዳይ ነው። የብልፅግና ፓርቲ የህዝብ ሉአላዊነት ተከብሮ የመንግስት ስልጣን በህዝብ ይሁንታና ውክልና በዴሞክራሲያዊ ምርጫ ብቻ ሊገኝ ይገባል ብሎ ያምናል። ፓርቲያችን ዴሞክራሲ የህዝብ ወኪሎች ከሚመረጡበት የምርጫ ሂደት አልፎ በይዘቱና ውጤቱም የህዝቦች እኩልነት፣ ነፃነትና ውክልና የሚጎለብትበት እንዲሆን ይታገላል። የብልጽግና ፓርቲ ዲሞክራሲ በትምህርት፣ በጤና፣ በመሠረተ ልማት ግንባታ በመታጀብ አሰላሳይ፣ ሞጋችና ፈጣሪ ኅብረተሰብ በመገንባት ረገድ አስተዋፅዖ ሊኖረው ይገባል ብሎ ያምናል። በመሆኑም የምንገነባው ዲሞክራሲ ተቋማዊ መሠረቱ ጽኑ እንዲሆንና ዲሞክራሲያዊ እሴቶች ተቋማዊ እንዲሆኑ ወደ ባሕልነት ደረጃ እንዲያድጉ ፓርቲያችን ይሰራል። በሀገራችን አስተማማኝና ዘላቂ ዲሞክራሲያዊ ሥርዓት ተመሥርቷል ልንል የምንችለው የፖለቲካ እንቅስቃሴዎች በአስተማማኝና

Addis Standard

ጠንካራ ተቋማዊ እና ዲሞክራሲያዊ ባህል መሠረት ላይ ሲታነጽ እና ሥርዓቱ ራሱን እያጠነከረ መደበኛ ሂደት ውስጥ በመግባት የማይቀለበስበት ደረጃ ላይ ሲደርስ ነው። ይህ የማይቀለበስ የዲሞክራሲ ጉዞ ብዙ አመታትን ሊፈጅ የሚችልና በመሰናክሎችም የታጀበ ውጣ ውረድ ያለው መሆኑን በመገንዘብ ፓርቲያችን ጽኑ ትግል ያደርጋል።

2.2.2.2 የምንገነባው የዲሞክራሲ ሥርዓት የግለሰብ መብቶችንና የቡድን መብቶችን ሳያበላልጥ የሚያስከብርና ሁለቱንም የመብት ዓይነቶች ለማስከበር በየባሕሪያቸው ልክ የተቀየሰ አቅጣጫን ይከተላል። ፓርቲያችን በንድፈ-ሃሳብ ደረጃ በሁለቱም መካከል ውጥረት ሊኖር እንደሚችል ግንዛቤ ውስጥ የሚያስገባ ቢሆንም፤ በአተገባበር ረገድ ግን አንዱ ሌላውን ለማዳከም ወይም ለማሳነስ መዋል የለባቸውም ብሎ ያምናል። ይልቁንም መብቶቹ ተነጣጥለው ሊሄዱ እንደማይችሉ፣ የግለሰብ መብትን በተሟላ መልክ ለማክበር ለቡድን መብቶችም እኩል እውቅና እና ትኩረት መስጠት እንደሚገባ፣ እንዲሁም የቡድን መብቶች በተሟላ ሁኔታ እንዲከበሩ ለማድረግ የግለሰብ መብቶችን የማክበር አስፈላጊነትን የሚያጎላ እንደሆነ ፓርቲያችን ያምናል። ይህን እውን ለማድረግም ፓርቲያችን እውነተኛ፣ ዲሞክራሲያዊ ፌደራላዊ ስርዓት ለማጠናከር በጽኑ ይታገላል። ፓርቲያችን የፌደራል ሥርዓቱ ዋና ምሰሶ ብዝሃነትን ማስተናገድ መቻሉ ነው ብሎ ያምናል። በመሆኑም ፓርቲያችን ለብሔር፣ ብሔረሰቦችና ህዝቦች ዕውቅና የሰጠ ፌደራላዊ ሥርዓት በመገንባት ኢትዮጵያ የብሔር፣ ብሔረሰቦችና ህዝቦች መብት የተከበረባት እውነተኛ ህብረ-ብሔራዊት አገር እንድትሆን ይሠራል። በአንጻሩም የግለሰብ መብቶችን በተመሳሳይ በሕገ-መንግስት ማዕቀፍ ሥር ማስከበር ይቻላል ብሎ ያምናል።

2.2.2.3 እንደ ኢትዮጵያ ብዝሃነት የሚንፀባረቅባቸው ሀገራት በፉክክር ላይ ብቻ የተመሰረተ ሳይሆን ትብብርንም የሚያካትት የዴሞክራሲ ስርዓት ተግባራዊ መሆን እንዳለበት ፓርቲያችን ያምናል። ስለዚህ ፓርቲያችን በትብብር ላይ የተመሰረተ፣ አካታች ዲሞክራሲያዊ ስርዓት እንዲገነባ ይሰራል።

2.2.2.4 ዲሞክራሲ ያለ ነጻ፣ ገለልተኛ እና ሙያዊ ብቃት ያላዳበሩ ተቋማት እውን ሊሆን እንደማይችል ፓርቲያችን በፅኑ ያምናል። ስለሆነም የዲሞክራሲ ግንባታ ሥራዎቻችን ለተቋማት ግንባታና አሠራር ቅድሚያ የሚሠጡና በዚያ ዙሪያ የሚያተኩሩ ይሆናሉ። ስለዚህም ፓርቲያችን የህዝብ አስተዳደር፣ የዲሞክራሲ፣ የሰላም እና የደህንነት እንዲሁም የህግ አስከባሪና የፍትህ ተቋማትን ለማጠናከር በትጋት ይሰራል። ፓርቲያችን የመከላከያ፣ የደህንነት እና የፖሊስ ተቋማት በዲሞክራሲያዊ መሰረት ላይ የታነጹ ነፃ፣ ገለልተኛ እና ለአገር እና ለህዝብ ጥቅም የቆሙ ወገንተኝነታቸው ለአገር ብቻ የሆኑ ተቋማት የማድረግ የሪፎርም ስራ በትኩረት ይሰራል። በዚህም ረገድ በየተቋማቱ ያለውን የሙያ ብቃት እና ክህሎት፣ እንዲሁም አደረጃጀት ከአካባቢው ሁኔታ እና ከዘመናችን የቴክኖሎጂ እድገት ጋር አቀራኝቶ ተቋማቱን ለማጠናከር በትኩረት ይሰራል። እነዚህ ተቋማት የተጣለባቸውን ህዝባዊ አደራ እና ሀላፊነት

Addis Standard

በአግባቡ እንዲወጡ የየተቋማቱን ባህሪ እና ተልዕኮ ማዕከል ያደረገ፣ በእውቀት የሚመራ፣ለየዘርፉ ልዩ ባህሪ ትኩረት የሚሰጥ ፣ለአመራር ብቃት ልዩ ትኩረት የሚሰጥ ያልተማከለ የተቋማት ሪፎርም እንቅስቃሴ ተግባራዊ ያደርጋል።

2.2.2.5 ፓርቲያችን ማንኛውም ፖለቲካዊ፣ ርዕዮተ-ዓለማዊ፣ ህጋዊ ወይም ሌሎች እንቅስቃሴዎች ሁሉ ህገ-መንግስትን የተከተሉ እንዲሆኑ ያደርጋል። የህግ አውጭው፣ የሕግ አስፈጻሚው እና የሕግ ተርጓሚው የስልጣን ከፍፍል በአግባቡ ተፈጻሚ እንዲሆንና የእርስ በርስ ቁጥጥርና ሚዛን እንዲጠናከር፣ የመንግስት አካላት ተጠያቂነትን እንዲረጋገጥ፣ ሕግ አውጭውን የሚያጠናክሩና የዳኝነት አስተዳደሩን የሚያጎለብቱ አሰራሮች ይዘረጋል። ፓርቲያችን ህገ መንግስቱ መሻሻል ያለበት በህገ መንግስታዊ መንግድ ብቻ ነው ብሎ ያምናል።

Addis Standard

## ክፍል ሦስት

## 3. የኢኮኖሚ ፕሮግራም

### 3.1 የኢኮኖሚ ፕሮግራም አላማ፡ ልማትና ፍትሃዊ ተጠቃሚነትን የሚያረጋግጥ አካታች የኢኮኖሚ ስርዓት መገንባት

የብልጽግና ፓርቲ በኢኮኖሚ ፕሮግራሙ የህዝባችን ሰፊ ክፍል የሆነውን ወጣት፣ አርሶ አደር፣ አርብቶ አደር እንዲሁም የከተማ ደሀ ህብረተሰብ ክፍልን ማዕከል ያደረገ አካታች የኢኮኖሚ ስርዓት በመገንባት የህዝባችንን የጋራ ኢኮኖሚያዊ ብልጽግናን የማረጋገጥ አላማ ይኖረዋል። ፓርቲያችን በሀገራችን ምርታማነትን እና ፍትሃዊ ተጠቃሚነትን ለማረጋገጥ መንግስት ወሳኝ አቅምና መሳሪያ ነው ብሎ ያምናል። በመሆኑም የመንግስት በኢኮኖሚው ስርዓት ውስጥ ያለው ተሳትፎ የገበያ መርህን በመከተል ስትራቴጂካዊ በሆነ ሁኔታ ሃብት የሚፈጥር፣ በተረጋጋ የማክሮ ኢኮኖሚ አስተዳደር ማዕቀፍ ውስጥ የግሉን ዘርፍና ሌሎች የኢኮኖሚ ተዋናዮች ተሳትፎ በማጎልበት ምርታማነትን በላቀ ደረጃና ቀጣይነት ባለው መልኩ የሚያሳድግ እንዲሆን ያደርጋል። በዚህም መሰረት ፓርቲያችን ጥራት ያለው እና ፈጣን ዕድገትን እንዲሁም ፍትሃዊ ተጠቃሚነትን ያረጋገጠ ኢኮኖሚ በመገንባት ሀገራችንን ወደ ብልፅግና ጎዳና ለማሸጋገር ያልማል።

### 3.1.1 የኢኮኖሚ ፕሮግራም ግቦች

#### 3.1.1.1 የብዝሃ ዘርፍ ኢኮኖሚ መዋቅር መገንባት

3.1.1.1.1 በአንድ ክፍለ ኢኮኖሚ ዘርፍ ላይ የተመሰረተ የኢኮኖሚ መዋቅር ዘላቂ እድገትንም ሆነ ፍትሃዊ ተጠቃሚነትን እንደማያረጋግጥ ፓርቲያችን ያምናል። ስለሆነም ሀገራችን አንጻራዊ እምቅ አቅሞችን ታሳቢ በማድርግ በግብርናው ዘርፍ ላይ ጥገኛ የሆነውን የሀገራችን ኢኮኖሚ ወደ ኢንዱስትሪ እና ሌሎች ተዛማጅ ዘርፎች ደረጃ በደረጃ እንዲሻገር በማድረግ ኢኮኖሚያችን በብዝሃ ዘርፍ የተዋቀረና ዘላቂ እድገት ያለው እንዲሆን ይሰራል። ይህን ለማሳካት ፓርቲያችን ሀገራችን እምቅ ጸጋ የታደለችባቸው ክፍለ ኢኮኖሚዎችን ሙሉ አቅም አሟጦ ወደ ልማት የማስገባት የኢኮኖሚ አቅጣጫን ይከተላል።

3.1.1.1.2 ፓርቲያችን ሀገራችን ለግብርና ዘርፍ ያላትን የስነ ምህዳር ተስማሚነት፣ የመሬት እና ሰፊ የሰው ሀብት በሙሉ አቅም ሥራ ላይ እንዲውል በማድረግ ልማትን ለማምጣት፣ የምግብ ዋስትና ለማረጋገጥ፣ የወጭ ንግድ ተወዳዳሪነት ለማረጋገጥ በትጋት ይሰራል። ይህም እንዲሆን ለማድረግ የግብርና ዘርፉ በግብዓት አቅርቦት፣አመራረትና የገበያ ትስስር መሰረት ያደረገ ግብርናን የማዘመን ስራ ይሰራል። ግብርናችን የአየር ንብረት ተጽእኖን የሚቋቋም እንዲሆን

Addis Standard

የተፈጥሮ ሀብት ጥበቃ ማጠናከርን ያካተተ አመራረት እንዲከተል ያደርጋል። የአርብቶ አደሩን ፍትሃዊ ተጠቃሚነት ለማረጋገጥ የተቀናጀና ዘመናዊ የአርብቶ አደሮች አከባቢ ልማት ይዘረጋል።

3.1.1.1.3 ኢንዱስትሪ የጠንካራና ዘመናዊ ኢኮኖሚ መሰረት እንደመሆኑ ዘርፉ በሀገራችን ኢኮኖሚ የሚሸፍነው ድርሻ እንዲሰፋ ፓርቲያችን በቁርጠኝነት ይሰራል። የኢንዱስትሪ ልማታችን ዋነኛ መርህ ኤክስፖረት መር ይሆናል። ሆኖም ግን ፓርቲያችን ሀገራችን የምታስገባቸውን የውጭ ሸቀጦች በሀገር ውስጥ ምርት የመተካት ፖሊሲን የውጭ ንግዳችንን ከማሳደግ ጋር አስተሳስሮ ይተገብራል። ይህም እንዲሆን ዘርፉ ከሌሎች ዘርፎች ጋር ጠንካራ የኋልዮሽና የፊትዮሽ ትሰስር እንዲኖረው የሚያደርግ፣ ተወዳዳሪነትን እና ምርታማነትን የሚያሳደግ አቅጣጫን ይከተላል። የኢኮኖሚ ሽግግርን ለማፋጠን የግብርና እና ኢንዱስትሪ ዘርፉን ትስስር የሚያጠናክርና ሀገራችንን በአምራች ኢንዱስትሪው ዘርፍ ቀዳሚ ማዕከል እንድትሆን የሚያስችል ስራዎችን በስፋት ይሰራል። ስለሆነም ዘርፉን ለውጭ እና ለሀገር ውስጥ ኢንቨስተሮች ሳቢ፣ ትርፋማና አዳጊ ሊያደርጉ የሚችሉ ፕሮግራሞችን በመቅረጽ፣ ምቹ የኢንቨስትመንትና ንግድ ከባቢን በመፍጠር እና የኢንዱስትሪ ሰላም በማስፈን ጠንካራ የኢንዱስትሪ ክፍለ ኢኮኖሚ ለመገንባት ፓርቲያችን ይሰራል።

3.1.1.1.4 ሀገራችን ያላትን የማዕድን ሀብት በልክ እና ቀጣዩን ትውልድ በማያራቁት መልኩ ለመጠቀም የማዕድን ጥናት፣ ፍለጋ እና ማውጣት እንዲሁም ለገበያ ማቅረብ ላይ ባለሀብቶች በተለይም የሀገር ውስጥ ባለሀብቶች በተናጥልም ይሁን ከመንግስት ጋር በመተባበር እንዲሳተፉ ፓርቲያችን ሁኔታዎችን ያመቻቻል። የማዕድን ፍለጋ እና የማውጣት ስራ የአካባቢው ማህበረሰብ ላይ የደህንነት ስጋት የማይጥል እንዲሁም ተጠቃሚነቱንም የሚያረጋግጥ እንዲሆን ፓርቲያችን በዘላቂነት ይሰራል። በመሆኑም በግለሰቦችም እና በማህበራት የሚደረግ በባሕላዊ መንገድ ማዕድን የማውጣት እና ለገበያ የማቅረብ ስራ ዘመናዊነትን እንዲላበስ በማድረግ የኢኮኖሚ አበርክቶቱ ከፍ እንዲል ይሰራል።

3.1.1.1.5 የአገልግሎት ዘርፍ በባህሪው በአንድ በኩል በራሱ እንደ ኢኮኖሚ ዘርፍ የስራ እድልና ሀብት የሚፈጥር ሲሆን በሌላ በኩል ደግሞ ለሌሎች የኢኮኖሚ ዘርፎች ከፍተኛ የሆነ የአስቻይነት ሚና ይጫወታል። በመሆኑም ፓርቲያችን ሀገራችን ከአገልግሎት ዘርፉ መንትያ የኢኮኖሚ ጥቅም ተጠቃሚ እንድትሆን ይሰራል። በዚህም ረገድ የቱሪዝም ዘርፉን በማልማት እና በማዘመን እንዲሁም የቱሪዝም አማራጮችን በማስፋት ሀገራችን በአፍሪካ ካሉ ዋና ዋና የቱሪስት መዳረሻዎች አንዷ እንድትሆን ፓርቲያችን ጠንክሮ ይሰራል። ይህንንም ለማድረግ የሀገራችንን ተፈጥሯዊ፣ ታሪካዊና ሰው ሰራሽ መስህቦችን የማስተዋወቅ እንዲሁም ለቱሪስት ፍሰትና ቆይታ ወሳኝ የሆኑ አገለግሎቶችን የሚያሳድጉ እና ለቱሪስት ምቹ የሚያደርጉ የቱሪዝሙን ዘርፍ የሚያዘምኑ ሥራዎችን ነድፎ ይንቀሳቀሳል። በመሆኑም በዘርፉ ተወዳዳሪነትን እና ቅልጥፍናን ከፍ ለማድረግ እንዲሁም አማራጮችን ለማስፋት የግሉን ዘርፍ ተሳትፎ ለማበረታታ ምቹ ሁኔታዎችን ይፈጥራል። የቱሪዝም

Addis Standard

መስህቦች ባሉባቸው አከባቢዎች የሚኖሩ ማህበረሰቦችን ከዘርፉ የሚጠቀሙበትን ሁኔታ ለማረጋገጥ ፓርቲያችን ይሰራል።

3.1.1.1.6 ፓርቲያችን የኢኮኖሚ ሴክተሮችን ውጤታማነትና ቅልጥፍና ለማሳደግ የሎጅስቲክስ መሰረተ ልማት እና ቁሶች አቅርቦትን በማሟላት ፈጣን እና በውድድር የሚመራ የሎጅስቲክስ አገልግሎት ስርዓት ለመዘርጋት ይሰራል። ይህም የሎጅስቲክስ ስርዓቱ በቴክኖሎጂ የተደገፈ እና በሰለጠነ የሰው ሀይል የሚመራ እንዲሆን ያደረጋል። የሎጀስቲክ ስርዓቱ ቀልጣፋ እና ውጤታማ እንዲሆን በሚደረገው ጥረት ውስጥ ሀገራችን የባህር በር አልባ በመሆኗ የሚያጋጥሙ የወደብ አገልግሎት ችግር ለመፍታት እንዲቻል ከጎረቤት ሀገራት ጋር በጋራ ለመስራት የሚያስችሉ ስምምነቶች እና ወጥ የሆኑ ስርዓቶች እንዲተገበሩ ከማድረግ በተጨማሪ የባህር ወደብ በጋራ የማልማት እና አገልግሎት የመስጠት ኢንቨስትመንቶች ላይ ተሳትፎ በማደርግ የሀገራችንን ጥቅም ለማስከበር ይሰራል።

## 3.1.2 **ጥራት ያለው የኢኮኖሚ ልማት እና ምርታማነትን መሰረት ያደረገ ማህበራዊ ፍትህ ማረጋገጥ**

3.1.2.1 ልማትን የሚያሳልጥና በየደረጃው ለሕዝቡ ፍትሐዊ በሆነ መንገድ ተደራሽ የሚሆን የኢኮኖሚና ማህበራዊ መሰረተ ልማት መኖር ለአገራችን በእጅጉ አስፈላጊ መሆኑን ፓርቲያችን በጥብቅ ያምናል፡፡ መዚህም መሰረት በመንግስት፣ በመንግስትና በግል በለሃብት ትብብር እና በግል ባለሃብት መዋዕለ ነዋይ ጥራት ያላቸው መሠረተ ልማቶች እንዲገነቡና በሁሉም የአገሪቱ አከባቢዎች ፍትሐዊ በሆነ መንገድ ሕዝቡ ተጠቃሚ እንዲሆን ፓርቲያችን በጥብቅ ይሠራል፡፡

3.1.2.2 ፓርቲያችን በፌደራል ስርዓቱ ማእቀፍ የበጀት ድልድል፣ የመሰረተ ልማትና የማህበራዊ ልማት ግንባታና ድልድል እንዲሁም ማንኛውም የሃብት አጠቃቀም የሁሉንም ህዝቦች ፍትሃዊ ተጠቃሚነት ባረጋገጠ ሁኔታ እንዲፈጸምና የነበሩ ፍትሃዊነት የጎደላቸውን አሰራሮችና አፈጻጸሞች ለማረምና ለማስተካከል ይሰራል።

3.1.2.3 ፓርቲያችን የቀደሙ የእድገት ስኬቶችን ጠብቆ በማስፋት፣ አድገቱ ጥራት ያለው እንዲሆን የነበሩ የአካታችነት እና የዘላቂነት ችግሮችን በማስተካከል ምርታማነትን በማረጋገጥ፣ የግሉ ዘርፍ በኢኮኖሚው ያለው ሚና የላቀ እንዲሆን በማድረግ፣ ከከፍተኛ የዕዳ ጫና የተላቀቀ እና ጤናማ የፋይናንስ ሂደትን የተከተለ ኢኮኖሚያዊ ስርዓትን ይገነባል። መንግስት መር ሆኖ የቆየውን እድገት ዘላቂነቱን ለማረጋገጥ የግሉ ክፍለ ኢኮኖሚ የሚኖረው ሚና አሁን ከሚገኝበት አነስተኛ ተሳትፎ ወደ ላቀ ደረጃ ከፍ እንዲል ያደረጋል። የመንግስትና የግል ዘርፍ ሚና ሚዛኑን ጠብቆ ማስኬድ የሚያስችል የኢኮኖሚ ፖሊሲ ማሻሻያዎች በስፋት ተግባራዊ እንዲሆኑ ያደርጋል። የግሉ ክፍለ ኢኮኖሚ ምርታማነቱን ለማሳደግ የሚያስችሉ የማክሮ-ኢኮኖሚ መረጋጋትን የሚያመጡ እና የቢዝነስ አመቺነትን የሚፈጥሩ ሰፊ የኢኮኖሚ ማሻሻያዎችን ተግባራዊ ያደረጋል። በተጨማሪም

Addis Standard

የአርሶና አርብቶ አደር ህዝባችን ከኢኮኖሚ እድገቱ ፍትሃዊ ተጠቃሚ እንዲሆን በተጨባጭ የሚያስችሉ ፖሊሲዎችን ይተገብራል፡፡

3.1.2.4 ኢኮኖሚ እንቅስቃሴዎች ከአካባቢ ጋር የተስማሙና የብዝሃ-ህይወት ሚዛንን የጠበቁ እንዲሆኑ የሚያስችል የአረንጓዴ ልማት ስትራቴጂ ተግባራዊ ያደርጋል፡፡ በዚህም በተፈጥሮ ሀብት የታደለችው ሀገራችን በልዩ ሁኔታ ተጠቃሚ እንድትሆን የሚያደርጋትን የዝቅተኛ ካርቦን ልቀት እና የታዳሽ ሀይል ልማት ላይ የግሉ ዘርፍ ተሳትፎ እንዲያድግ በማድረግ በሀገራችን የአረንጓዴ ኢኮኖሚ እንዲያብብ እንሰራለን፡፡

3.1.2.5 የምናስመዘግበው የኢኮኖሚ እድገት ጠቅላላ ሀገራዊ ምርትን ከማሳደግ ባሻገር የህዝቦችን ሰብዓዊ ልማት የሚያመጣ መሆን እንዳለበት ፓርቲያችን ያምናል፡፡ በመሆኑም ኢኮኖሚያችን ለሁሉም የኢኮኖሚ ተዋንያን ፍትሃዊ እና በሁሉም የሃገሪቱ አከባቢዎች ተመጣጣኝ የእድገት እድልን የሚፈጥር፣ የእድገት ምጣኔው እየሰፋና ግለቱን ጠብቆ የሚዘልቅ፣ ጥራቱን የጠበቀና በቀጣይ ትውልድ ኪሳራ ላይ የማይገነባ መሰረተ-ፅኑ የኢኮኖሚ እድገት ለማስመዝገብ ፓርቲያችን ይሰራል፡፡

3.1.2.6 ፓርቲያችን በተለያዩ ሀገራትና ዓለም ክፍሎች ከሚፈጠሩ የኢኮኖሚ ቀውሶች የሚመጡ ጫናዎችን የሚቋቋም የተረጋጋ ማክሮ ኢኮኖሚ ያለው ብሔራዊ ኢኮኖሚ መገንባትን ያልማል፡፡ ይህንንም ለማድረግ ፓርቲያችን ሀገራዊ ፍላጎት እና አቅርቦትን ለማጣጣም ትኩረት ሰጥቶ ይሰራል፡፡ ይህም ጥቅል የሐገር ውስጥ ምርትን ማሳደግ፣ ለኢኮኖሚ እድገት የሚረዳ ሰፊ የገበያ ፍላጎትን መፍጠር ብሎም የኑሮ ውድነትን መቆጣጠር ላይ ያተኮረ ሆኖ ውጤታማ የማክሮ ኢኮኖሚ ትንበያ፣ ፖሊሲ ቀረጻ እና ማስፈጸም ላይ የሚያጠነጥን አቅም ግንባታ ላይ አተኩሮ ይሰራል፡፡ በዚህም መሰረት ተቀባይነት ያለው እና የተረጋጋ የዋጋ ግሽበት፣ የተረጋጋ የወለድ ምጣኔ፣ ዝቅተኛ የእዳ ጫና፣ አነስተኛ የበጀት ጉድለት፣ በቂ የውጭ ምንዛሪ ክምችት እንዲሁም የተረጋጋ የመገበያያ ገንዘብ ተመን እንዲኖር ይሰራል፡፡

3.1.2.7 የፋይናንስ ዘርፉ በቆጣቢ እና በኢንቨስተር የኢኮኖሚ አሃዶች መካከል የሚኖርን የገንዘብ መጠን ፍላጎት በማስታረቅ ለኢኮኖሚ እንቅስቃሴ ወሳኝ ሚና ያለው መሆኑን ፓርቲያችን በጽኑ ያምናል፡፡ ስለዚህም ዘመናዊ አሰራርና ተወዳዳሪነት የሰፈነበት መሠረታዊ አቅጣጫዎች ላይ ያተኮረ የፋይናንስ ዘርፍ ሪፎርም ያደርጋል፡፡ ይህም ሲሆን በሁሉም የኢኮኖሚ ደረጃ ላይ ያሉ የህብረተሰብ ክፍሎችን አካታች የሆነ የፋይናንስ አገልግሎት በማስፋፋት እና ተደራሽ እንዲሆን በማድረግ የዜጎችን የኢኮኖሚ አቅም ማጎልበት ላይ ትኩረት በማድረግ ይሰራል፡፡

### 3.1.3 ***ሀብት ፈጠራን የሚያሳድግ እውቀት መር ኢኮኖሚ መገንባት***

3.1.3.1 ዘላቂ እና አስተማኝ ብልጽግና የሚረጋገጠው ኢኮኖሚው እውቀትን እንደ ግብዓትም ሆነ እንደምርት የሚጠቀም ሆኖ ሲገነባ እንደሆነ ፓርቲያችን ይገነዘባል፡፡ በመሆኑም በቴክኖሎጂ

Addis Standard

እድገት፣ በኢኖቬሽ እና በሰው ሀይል ልማት ላይ ያተኮረ የእድገትና የልማት አቅጣጫ ከረጅምና መካከለኛ ጊዜ አኳያ መፈፀም ዋነኛ አላማው አድርጎ ይንቀሳቀሳል።

3.1.3.2 በሀገራችን ቀጣይነት ላለው ምርታማነትን እና የህዝብ ኑሮ ደረጃ ለማሻሻል ቁልፍ የሆነው እውቅት እና ሳይንሳዊ ምርምር ዝቅተኛ ደረጃ በመሆኑ እንደሆነ ይገነዘባል። በመሆኑም ፓርቲያችን እውቀትን መሰረት ያደረግ ቴክኖሎጂ፣ ቢዝነስ ፈጠራ እንዲሁም ዘመናዊ የአመራርነት ክህሎቶች እና ተቋማት ግንባታ ላይ ትኩረት የሚያደርግ ኢኮኖሚያዊ ማሻሻያ ያደርጋል።

3.1.3.3 ፓርቲያችን እውቀት መር ኢኮኖሚ የሚገነባው ለሰው ኃይል ልማት ከፍተኛ ትኩረት በመስጠት ነው ብሎ ያምናል። በመሆኑም ተወዳዳሪ፣ ምርታማና፣ ጤናማ የሰዉ ሃይል ልማት ላይ ትኩረት ያደርጋል። የኢኮኖሚዉን ነባራዊ ሁኔታ ያገናዘበና ገበያን መሰረት ያደረገ የሰዉ ኃይል ልማት ስትራቴጂ ተግባራዊ በማድረግ ብቁ እና ውጤታማ የሰው ሀይል በማልማት በእውቀት የሚመራ ኢኮኖሚ ለመፍጠር ፓርቲያችን ይሰራል።

### 3.1.4. ምቹ፣ ጽዱ እና አረንጓዴ ከተሞችን እውን ማድረግ

3.1.4.1 የተቀናጀ የከተማ ልማትን ለማፋጠን የተቀናጀ የከተሞች መሠረተ ልማቶችን አቅርቦት እና ሙያዊ ብቃትን መሠረት ያደረገ ጠንካራ የከተማ አስተዳደር እንዲኖር ፓርቲያችን ይሰራል። ከተሞች ብቃት ያለው የፋይናንስ ሥርዓት እንዲኖራቸው በማስቻል መሠረታዊ የሆኑ የማዘጋጃ ቤት አገልግሎቶች ማለትም የመንገድ፣ የቆሻሻ ማስወገጃ፣ የውሃ፣ የመብራትና ሌሎች አገልግሎቶችን በጥራት ለህብረተሰቡ ማቅረብ እንዲችሉ ያደርጋል። ከተሞች ለኑሮ ምቹ እንዲሆኑ ጽዱ እና አረንጓዴ ለማድረግ ፓርቲያችን ህብረተሰቡን ያስተሳሰረ ከተሞችን ጽዱ እና አረንጓዴ የማድረግ ስራ ይሰራል።

3.1.4.2 ሁሉን አቀፍ የካዳስተር ሥርዓት ተግባራዊ በማድረግ የከተማ ቦታ ምዝገባን ማዘመን፣ ዘመናዊና የከተሞችን የዕድገት ሁኔታ ያገናዘበ የመሬት ልማትና አስተዳደር የመረጃ ሥርዓት በመዘርጋት የከተማ መሬት አቅርቦትንና አጠቃቀም ግልጽ፣ ልማትን የሚደግፍ እና ቀልጣፋ እንዲሆን ይደርጋል።

3.1.4.3 ህብረተሰቡን ባሳተፈ መልኩ በከተሞች የሥራ ዕድል ፈጠራና የምግብ ዋስትና ማረጋገጥ፤ በግል ዘርፍ ሰፊ ተሳትፎ የከተማ ቤት ልማትና አስተዳደር ሥራዎችን ማጠናከርና የተቀናጀ የከተሞች መሠረተ ልማቶችን ያቀርባል።

3.1.4.4 ፓርቲያችን የገጠር ልማትንና የከተማ ልማትን በማቀናጀትና በማስተሳሰር ዜጎች በያሉበት በአገራዊ ልማቱ የነቃ ተሳትፎ እንዲኖራቸውና ፍትሃዊ ተጠቃሚነታቸው እንዲረጋገጥና እንዲሁም ከግብርና  ልማት ወደ ኢንዱስትሪ ልማት የሚደረገው መዋቅራዊ ሽግግር እንዲፋጠን በትኩረት ይሰራል።

Addis Standard

3.1.4.5 ፓርቲያችን ከተሞችን ከ ከተሞች፣ ክልሎችን ከክልሎች እንዲሁም ሀገራችንን ከጎረቤት ሀገራት ጋር በሚያዋስኑን ስፍራዎች በጥናት ላይ የተመሰረቱ የልማት፣ ኢኮኖሚ ትሥሥር እና የከተሜንት ኮሪደሮች በመለየና በማልማት አንድ የኢኮኖሚ ማህበረሰብ ለመፍጠር ይሰራል።

Addis Standard

ክፍል አራት

## 4. ማኀበራዊ ፕሮግራም

### 4.1 የማህበራዊ ፕሮግራም አላማ፡ ሁለንተናዊ ብልጽግናን የሚያረጋግጥ አካታች ማህበራዊ ልማት

ሀገራችን ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ዕድገት መነሻዋ ዝቅተኛ ደረጃ በመሆኑ ሁለንተናዊ ማህበራዊ ብልጽግና የማረጋገጥ ጉዳይ የፓርቲያችን ማህበራዊ ፕሮግራም ማጠንጠኛ እምብርት ይሆናል። በመሆኑም የማኀበራዊ ልማት ስራዎቻችን የእድገትና ፍትሃዊ ተጠቃሚነት መንትያ ግቦችን የማሳካት ጉዳይ ይሆናል። የማህበራዊ ልማት ሥራዎቻችን ከችሮታና ከነባሩ የማህበራዊ ደህንነት ትኩረት ወጥቶ ችግሩን ከመብት አንጻር የሚመለከተው ይሆናል። ማህበራዊ ብልጽግናን ለማረጋገጥ የሚደረገው ጥረት ተደራሽነትና አካታችነትን ባለው መልኩ የማህበረሰብን ጤና፣ ደህንነት እና ምቾት የሚያስጠብቅ መሆን ይኖርበታል። የማህበራዊ ፕሮግራማችን ዜጎችን የሚስተሳሰረን፣ ከችግርና መከራ የሚታደጋቸው፣ የሀገርን አለኝታነት የሚያሰርጽ እና በሀገራችን አወንታዊ ሰላምን የሚያረጋግጥ ይሆናል። የማኀበራዊ ልማት ፕሮግራማችን ህብረ ብሄራዊ ማንነትን መሰረት ያደረገ ሀገራዊ አንድነትን የሚያጎለብቱ እንዲሆኑ ዒላማ አድርጎ መንቀሳቀስ የፓርቲያችን ማህበራዊ ፕሮግራማ አላማ መገለጫ ይሆናል።

### 4.2 ጥራት፣ ፍትሐዊነትና አግባብነት ያለው የትምህርት ስርዓት መዘርጋት

**4.2.1** ፓርቲያችን በዋናነት የትምህርት ተደራሽነትን አስጠብቆ፤ በሁሉም የትምህርት ደረጃዎች የትምህርት ጥራትን ማሳደግ የትምህርት ፕሮግራሙ ዋነኛ አላማ አድርጎ ለውጤቱ ይተጋል። ተደራሽነቱን ለማስፋት እና መሃይምነትን ለማጥፋት፣ ፍትሀዊነት እና አግባብነትንም ለማረጋገጥ በትኩረት ይሰራል።

**4.2.2** ፓርቲያችን ሁሉም የትምህርት ተቋማት የአካዳሚ ነጻነትን ከሚያቀጭጩ እና በዕለት ተዕለት የመማር ማስተማር፣ የአስተዳደርና የምርምር ስራ ከፖለቲካዊም ሆነ ከአስተዳደራዊ ጣልቃ ገብነቶች ነጻ እንዲሆኑ በማድረግ ሁሉም እይታዎች በእኩል መድረክ አግኝተው በነጻነት የሚንሸራሸሩባቸው እንዲሆኑ ይሰራል።

**4.2.3** መምህራን በተሻለ ችሎታና ስነ ምግባር የታነፁ ሆነው ትውልድን በእውቀት እና በስነ-ምግባር ቀራጮች እንዲሆኑ ፓርቲያችን ይሰራል። ከዚህም ጋር ተያይዞ መምህራን የሚገባቸውን ክብርና ጥቅም እንዲያገኙ የኑሮ ደረጃቸውም እንዲሻሻል የሚያስችሉ ፕሮግራሞች ተግባራዊ ያደርጋል።

**4.2.4** የስነ-ምግባርና ስነ-ዜጋ ትምህርት አብሮነትን በማሳደግና ግብረ ገባዊ እሴቶችን በማስፋትና በማስረፅ በመልካም ስነ-ምግባር የታነፀ ሀገር ወዳድ ትውልድ በማፍራት ረገድ የሚጫወተው ሚና እጅግ የላቀ

Addis Standard

እንደሆነ ፓርቲያችን ይረዳል። ስለዚህ የስነ-ምግባርና ስነ-ዜጋ ትምህርት ሀገራዊ አብሮነትን እና ህብረ ብሄራዊነትን የሚያጠናክር፣ የሀገር ፍቅርን የሚያፀና እና ግብረ-ገብነት የተላበሰ ትውልድን መፍጠሪያ ተደርጎ እንዲቀረፅ ያደርጋል።

**4.2.5** ፓርቲያችን የቅደመ-መደበኛና መደበኛ ትምህርት በሀገራችን ሙሉ ለሙሉ እንዲዳረስ ትኩረት ሰጥቶ የሚሰራ ቢሆንም ትኩረት ሳይሰጠው የቀረውን የቅድመ መደበኛ ትምህርትን ለማሳደግ የተለየ ትኩረት ሰጥቶ ይሰራል።

**4.2.6** ፓርቲያችን ትምህርቶች የተግባር ተኮር ትምህርትና የመስክ ልምምድ ፕሮግራሞች በትምህርት ፕሮግራም ውስጥ እንዲያካትቱ ከማድረግ ባሻገር ተግባራዊ እንዲሆኑ ይከታተላል። ይህ እንዲሆን በማድረግም የሀገራችን ከፍተኛ ትምህርት ከኢንዱስትሪው የሰው ሀይልና የምርምር ፍላጎት ጋር ያለውን ትስስር ከፍ እንዲል የሚያደረጉ አቅጣጫዎችን ይተገብራል። የከፍተኛ ትምህርት ቅበላ ስርዓቱ የተማሪዎችን ፍላጎትና ዝግጁነት ግምት ውስጥ ያስገባና የኢኮኖሚውን ፍላጎትና አቅም ባገናዘበ መልኩ እንዲቀረፅ ያደርጋል።

**4.2.7** ዩኒቨርሲቲዎች የዜጎችን ህይወት መሻሻልን የሚሰብኩ የእውቀትና ጥበብ መናሃሪያዎች፣ ብዝሃነትን የሚያጎለብቱና እርስ በእርስ መቀራረብን የሚፈጥሩ የአለማቀፋዊ እሴቶችና አስተሳሰቦች ማዕከላት እንዲሆኑ ፓርቲያችን አበክሮ ይሰራል።

**4.2.8** በመጀመሪያ እርከን የትምህርት ቋንቋ ብዝሃ ልሳን እንዲሆን የሚያደርግ ሲሆን ብዝሃ ልሳንነቱ የምንገነባውን ህብረ ብሄራዊ አንድነትን ታሳቢ ባደረገ መልኩ በሁሉም ክልሎች ከክልሎች ነባራዊ ሁኔታ ጋር በሚጣጣም መልኩ ተግባራዊ እንዲሆን ያደርጋል።

**4.2.9** የትምህርት ስርዓቱ ከቴክኖሎጂ ጋር የተዋወቀ ቴክኖሎጂንም የሚያስተዋውቅ እንዲሆን ይደረጋል። በዚህም ትምህርት ቤቶች በቴክኖሎጅ የታገዙ እንዲሆኑ ከማድረግ ባሻገር ማህበረሰባችን ውስጥ የሳይንስ እና የቴክኖሎጂ እውቀት እንዲፈጠር እና እንዲስፋፋ ለማድረግ ይተጋል።

**4.2.10** የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ተቋማት፣ አቅማቸው እንዲጎለብት ተደርጎ ለኢንዱስትሪው የጀርባ አጥንት የሆነ ብቃት ያለው የሰው ኃይል እንዲያመርቱ ከማድረግ ባሻገር ለቴክኖሎጂ ሽግግር ሚናው ከፍ ያለ እንዲሆን ያደርጋል።

Addis Standard

## 4.3 መከላከልን መሰረት ያደረገ የጤና ስርዓት መዘርጋት

**4.3.1** በሽታን መከላከል ላይ የተመሰረተው የጤና ፖሊሲ ተጠናክሮ ይቀጥላል። ጎን ለጎን አክሞ የማዳን ዘርፉን ለማጠናከር በሙያቸውና በስነ-ምግባራቸው የላቁ ባለሙያዎችን ማፍራት ላይ ፓርቲያችን ቅድሚያ ይሰጣል።

**4.3.2** የህክምና ባለሙያዎች ፍልሰትን ለመከላከል ለባለሙያዎች ልዩ ማበረታቻ እና ጥቅማጥቅም የሚሰጥ አሰራር ያዘጋጃል። በተለይም ከገጠረ ወደ ከተማ የሚደረግ የባለሙያዎችን ፍልሰት ለመቀነስ በገጠር የሚሰሩ ባለሙያዎችን ልዩ ጥቅምን ይሰጣል።

**4.3.3** የህክምና ቁሳቁስ እጥረትን ለመቀነስ ትኩረት ሰጥቶ ይሠራል። የህክምና ቁሳቁሶች በሀገር ውስጥ እንዲመረቱ የሚደረግበት አቅም እንዲፈጠር ፓርቲያችን ይሰራል።

**4.3.4** የባህል ህክምና እንዲዘምን ልዩ ትኩረት ሰጥቶ ከዘመናዊ ህክምና ጋር እንዲደጋገፍና በጥናትና ምርምር እንዲልቅ ያደረጋል።

**4.3.5** በዝቅተኛ የኑሮ ሁኔታ ያሉ ዜጎችንና የሀገር ባለውለታዎችን ታሳቢ ያደረገ የነጻ ህክምና አገልግሎት የሚሰጥበት አሰራር እንዲዘረጋ ያደረጋል። ከዚህም በተጨማሪ የጤና መድህን ሽፋን በመላ ሀገራችን እንዲዳረስ አሰራርን በማዘመን ሁሉም ኢትዮጵያዊ ደረጃውን የጠበቀ የጤና መድህን ሽፋን ተጠቃሚ እንዲሆን ያደረጋል።

**4.3.6** የኤች.አይ.ቪ. ኤድስ ስርጭት ለመግታት አዲስ ስትራቴጅ ነድፎ ይሠራል። የአዕምሮ ህክምና ላይ ልዩ ትኩረት በመስጠት የሕክምናና የማገገሚያ ማዕከላት እንዲስፋፉ ያደረጋል።

**4.3.7** ተላላፊ ያልሆኑ በሽታዎች ለመግታት ከሚደረጉ የቅድመ-መከላከል ስራዎች በተጨማሪ በሽታዎችን አክሞ ለማዳን የሚያስችሉ የሕክምና አገልግሎቶች እንዲስፋፉ ያደረጋል።

**4.3.8** ወረርሽኞችን በዘላቂ ሁኔታ ለመከላከል የሚያስችል ልዩ የወረርሽኝ መከላከል ሥርዓት ይዘረጋል።

**4.3.9** ሀገራችን በጤና ዘርፍ ወደ ኋላ የቀረችባቸዉን ዘርፎች አንዱ የሆነው የሕፃናት መቀንጨር ላይ በልዩ ትኩረት በመስራት የህፃናት መቀንጨር ዜሮ እንዲሆን ያደርጋል።

## 4.4 የሞኖሪያ ቦታ የማግኘት መብትን የሚያሟላ የቤቶች ልማት

**4.4.1** ፓርቲያችን የዜጎች መሰረታዊ ፍላጎት የሆነዉን የመጠለያ ጥያቄ ለማሟላት የመሬትና የፋይናንስ አቅርቦቶችን ለማመቻቸት ይሰራል።

**4.4.2** ፓርቲያችን ቤት ፈላጊዉ በማህበር ተደራጅቶ አቅሙን በማስተባበር ፍላጎቱን የሚያሟላበትን ሁኔታ የሚያመቻች አሰራርን ከመተግበር በተጨማሪ የሀገር ውስጥ ባለሀብቶች እና የውጭ ሀገር የሪል ስቴት አልሚዎች የዘርፉ ተሳትፎ እንዲጎለብት አሰራር ይዘረጋል።

Addis Standard

**4.4.3** የቤቶች ልማት ስርዓታችን የዘመነ እንዲሆን ዲጂታይዝድ የሆነ አሰራርን እውን ከማድርግ በተጨማሪ የፕሮጀክት ማኔጅመንት ስራዎች በእውቀት እና በስነ-ምግባር ላይ የተመሰረቱ በማድረግ በቤቶች ልማት ላይ ያለው የፕሮጀክት አስተዳደር ክፍተት በዘላቂነት እንዲቀረፍ ያደረጋል፡፡

**4.4.4** በየጊዜው እየናረ የሚገኘውን የቤት ኪራይ ዋጋ የተከራዩን የመክፈል አቅም ያገናዘበ እንዲሁም የአከራዩን ጥቅም በተመጣጣኝ ሁኔታ ያስጠበቀ በአጠቃላይ ፍትሃዊ እንዲሆን የሚያደርጉ ስራዎችን ይተገበራል፡፡

**4.4.5** በከተሞች በተለይም በጥናት በሚለዩ ዋና ዋና ከተሞች ለመንግስት ሰራተኞች፤ ዝቅተኛ ገቢ ላላቸው ዜጎች በአጭር ጊዜ ውስጥ ቤት የሚያገኙበት አሰራር ተግባራዊ ያደረጋል፡፡

## 4.5 የሀገራችንን ኢኮኖሚ ያገናዘበ የማኅበራዊ ጥበቃ ሥርዓት

**4.5.1** የማኅበራዊ ዋስትና ስርዓታችን ህዝባችንን ከአስከፊ ችግርና ከጉስቁልና ኑሮ በመጠበቅ ጤናማ ማህበረሰባዊ መስተጋብር እንዲኖር ትኩረት አድርጎ እንዲሰራ ያደረጋል፡፡ የሀገራችን ኢኮኖሚያዊ ዕድገትና አቅም ያገናዘቡ እና አካታች የሆኑ ልዩ ልዩ ጥራታቸውን የጠበቁ የማኅበራዊ ዋስትና ሥርዓቶችን ፓርቲያችን ይዘረጋል፡፡

**4.5.2** ለችግር ተጋላጭ የህብረተሰብ ክፍሎችን (ወላጅ አልባ ህፃናት፣ በልመና ተግባር የሚተዳደሩ፣ የጎዳና ተዳዳሪዎች፣ በወሲብ ንግድ የሚተዳደሩ፣ ስራ አጦች፣ ጧሪ የሌላቸው አዛውንቶች፣ ወዘተ) ለመደገፍ የሀገራችን ኢኮኖሚ ያገናዘቡ የማኅበራዊ ዋስትና ስርዓቶች ፓርቲያችን እንዲተገበሩ ያደርጋል፡፡

**4.5.3** የማኅበራዊ ዋስትና ሥርዓታችን በአደረጃጀቱና በአገልግሎት አሰጣጡ እንዲዘምን፣ እንዲሰፋ እና ሁሉ-አቀፍ እንዲሆን ያደረጋል፡፡ ይህንንም ለማድረግ በቴክኖሎጂ የታገዘ ዲጅታላይዝድ የሆነ አሰራር ይዘረጋል፡፡

**4.5.4** ለሀገር ውለታ የዋሉ ነገር ግን ችግር ላይ ያሉ ግለሰቦችንና ቤተሰቦቻቸውን በዘላቂነትና በተደራጀ መልኩ የሚረዱበትና የሚቋቋሙበት ስርዓት ተግባራዊ ያደርጋል፡፡

**4.5.5** የአካል ጉዳተኞችን ሁለንተናዊ መብት፣ ክብርና ደህንነት ለማስጠበቅ እንዲሁም በሁሉም የህይወት ዘርፎች ተሳትፏቸውንና ተጠቃሚነታቸውን ለማረጋገጥ በሙሉ ቁርጠኝነት ይሰራል፡፡ የአካል ጉዳተኞችን ጉዳይ በተሻለ ሁኔታ በመምራት አካል ጉዳተኞች እንደ ማንኛውም ዜጋ በሀገራቸው ሁለንተናዊ እንቅስቃሴ እኩል ተሳታፊና ተጠቃሚ እንዲሆኑ ይሰራል፡፡

**4.5.6** ልማታዊ ሴፍቲኔትን በሰፊው ተደራሽ ለማድረግና የምግብ ዋስትናን ለማረጋገጥ አዳዲስ ስትራቴጅዎችን ይተገበራል፡፡

Addis Standard

## 4.6 የሠራተኞችን መብት ማስከበርና የሥራ ሥነ ምግባር ማሳደግ

**4.6.1** አሰሪና ሰራተኛ በስራ ቦታ ጤናማ ማኅበራዊ ግንኙነት እንዲኖራቸውና የኢንዱስትሪ ሰላም እንዲሰፍን ለማድረግ ፓርቲያችን ይሰራል።

**4.6.2** ሰራተኛው ከኢንዱስትሪው ምርታማነት ፍትሐዊ ተጠቃሚ እንዲሆንና በነፃነት ተደራጅቶ የመንቀሳቀስ መብቱ ሙሉ ለሙሉ እንዲከበርለት ከማድረግ በተጨማሪ አሰሪውም ተገቢ ጥበቃ እንዲያገኝ ያደርጋል።

**4.6.3** የሥራ ቦታዎች ምቹና ጤናማ እንዲሆኑ የሚያደርጉ እንዲሁም አደጋን የሚቀንሱ መሠረታዊ ሁኔታዎች እንዲሟሉ የሚያስችል የቁጥጥር ሥርዓትን በማዘመን እና በመተግበር የሠራተኞችን ደህንነት የማስጠበቅ ሥራ ይሰራል።

## 4.7 የሴቶችን ተሳትፎና ተጠቃሚነት ማጎልበት

**4.7.1** የሴቶች ችግር እየተወሳሰበ እንዲመጣ እያደረጉ ያሉ ድብቅ ጾታዊ ጥቃትን ለመታገል ሴቶች ለመብታቸው እንዲታገሉ የሚያስችሉና የመደራደር አቅማቸውን የሚያሳድጉ ስትራቴጅዎች ነድፎ ይተገብራል።

**4.7.2** የሴቶች ኢኮኖሚያዊ ተጠቃሚነት አሁንም በሚፈለገው ልክ አለመሆኑ ፓርቲያችን ይረዳል። ፓርቲያችን ይህን ለማስተካከል በሁሉም የኢኮኖሚ ትግበራዎቻችን ላይ የሴቶችን ተጠቃሚነት ባስጠበቀ መልኩ እንዲተገበር ያደርጋል። በዋነኛነትም የሴቶች የስራ እድል፤ የብድር አቅርቦት፣ የመሬት ባለቤትነት፣ የመኖሪያ ቤት ተጠቃሚነት ላይ ሰፊ ስራ ይሰራል።

**4.7.3** የሴቶችን የፓለቲካ ተሳትፎ እና ውሳኔ ሰጪነት ለማሳደግ ከከፍተኛ አመራር እስከ ታችኛው የአመራር እርከን ድረስ የሴቶችን ተሳትፎ እንዲጎለብት ይሰራል።

**4.7.4** የሴቶችን ጤና ከመጠበቅ አንጻር ከቅድመ ወሊድ እስከ ድህረ ወሊድ ድረስ በአቅራቢያቸው በጤና ኬላ አገልግሎት እንዲያገኙ ያደረጋል። የሴት ልጅ ግርዛትን ለማስቀረት በቁርጠኝነት ይሰራል። ከሴቶች የስነ ተዋልዶ ጤና ችግር ለመቅረፍ አካታች የሆኑ ልዩ ልዩ ስራዎች ይተገበራሉ።

**4.7.5** በኑሮ አስገዳጅነት በወሲብ ንግድ ላይ የተሰማሩ ሴቶች ደህንነታቸው እንዲጠበቅና ሌላ አማራጭ የስራ ዘርፍ ላይ እንዲሰማሩ የሕግ፣ ተቋማዊ እና አስተዳደራዊ ስራዎች ተግባራዊ ያደርጋል።

## 4.8 የወጣቶችን ፖለቲካዊ፣ ኢኮኖሚያዊ እና ማህበራዊ ተሳትፎ እና ተጠቃሚነት ማስፋት

**4.8.1** ፓርቲያችን ወጣቶች ለሀገራችን የዲሞክራሲ ሂደት ተመልካች ሳይሆኑ ተዋንያን እንዲሆኑ በቁርጠኝነት ይሰራል። በዚህም የአመራርነት ክህሎታቸውን በየጊዜው እያሳደገ ከከፍተኛ አመራር ውሳኔ ሰጪነት እስከ ታችኛው የአመራር እርከን ድረስ ሰፊ ድርሻ እንዲኖራቸው ያደርጋል። ወጣቶች በነጻነት ተደራጅታቸው ለመብታቸው እንዲታገሉ አበክሮ ይሰራል።

Addis Standard

**4.8.2** አጠቃላይ ኢኮኖሚ እንቅስቃሴዎቻችን ወጣቱን ማዕከል ያደረጉ እንዲሆኑ ይሰራል። የወጣቶችን የስራ እድል በተመለከተ ወጣቶች በተማሩት የትምህርት ደረጃ፣ ባላቸው እውቀት፣ እንዲሁም በጥናት አዋጪ በሆኑ ዘርፎች ላይ እንዲሰማሩና ውጤታማ እንዲሆኑ ሰፋፊ የስራ አማራጮች ያቀርባል።

**4.8.3** የወጣቶችን የሱስ ተጠቂነትን ለመግታት ሱስ አምጭ እጾችን በጥናት ላይ ተመርኩዞ በህግ ለመቆጣጠር ከመስራት በሻገር የሱስ ማገገሚያ ማዕከላት እንዲስፋፉ ይሰራል። የስፖርት ማዘውተሪያዎችና የመዝናኛ ሥፍራዎችን በጥራትና በብዛት በማሳደግ ወጣቶች ንቁና ገብረ-ገብነትን የተላበሱ እንዲሆኑ ይሠራል።

**4.8.4** ወጣቶች የሚለያዩ ማንነት ቢኖራቸውም አንድ በሚያደርጋቸው ኢትዮጵያዊነት ላይ መግባባት እንዲፈጥሩ የወጣቶች የዜግነት አገልግሎት በህግ፣ ተቋማዊ እና አስተዳደራዊ እርምጃዎች ተደግፎ በመላ ሀገራችን ተግባራዊ እንዲሆን ያደረጋል።

**4.8.5** ፓርቲያችን ለወጣቶች የበለጸገች ኢትዮጲያን ለማስረከብና ወጣቱ ሀገር ወዳድ ዜጋ እንዲሆን ኢትዮጲያ በብዝሀነት የተሞላችና ይህም ብዝሀነታችን የጥንካሬያችን እና የእድገታችን መሰረት እንጂ የመለያየት እና የጥላቻ ምክንያት እንዳይሆን አበክሮ የሚታገልለት ግብ ሲሆን ወጣቶችን የትግሉ መሰረት አድርጎ ይሰራል።

## 4.9 ውጤታማና ተጨባጭ የስነ-ህዝብ ሥርዓት መዘርጋት

**4.9.1** ፓርቲያችን ለማኅበራዊ እና ኢኮኖሚያዊ ብልጽግና የስነ ህዝብ ፖሊሲ መሰረት ነው ብሎ ያምናል። ስለሆነም ለስነ ህዝብ ጉዳይ ከፍተኛ ትኩረት ሰጥቶ ይሰራል። ፓርቲያችን የህዝብ ቁጥሩ ከማኅበራዊና ኢኮኖሚያዊ እድገታችን ጋር ተመጣጥኖ እንዲሄድ የሚያደርጉ ስትራቴጂዎችን ይተገብራል።

**4.9.2** ጤናማ የሆነ ህብረተሰብ መፍጠር የሚያስችል የቤተሰብ ምጣኔ እና የወሊድ ቁጥጥር ፕሮግራሞች በተጠናከረ መልኩ ተግባራዊ ያደርጋል።

**4.9.3** የኢኮኖሚያዊ፣ ፖለቲካዊና ማህበራዊ እቅዶቻችን ውጤታማ በሆነ መልኩ ለመተግበር ያስችል ዘንድ የዘመነ የህዝብ ቆጠራና የህዝብ ቁጥር ትንበያ ስራዎች ላይ የተለየ ትኩረት ሰጥቶ ይሰራል።

## 4.10 ብዝሀነታችንን ማዕከል ያደረገ የቋንቋ ፖሊሲ

**4.10.1** የፓርቲያችን የስራ ቋንቋ ክልሎች በህገ መንግስታቸው የስራ ቋንቋ ይሆናል ብለው ያጸደቋቸው ቋንቋዎች ይሆናሉ።

**4.10.2** የሁሉም ብሄር፣ ብሄረሰቦችና ህዝቦች ቋንቋዎች እንዲያድጉና እንዲጎለብቱ የሕግ፣ ተቋማዊ እና አስተዳደራዊ ስራዎች ተገባራዊ ያደርጋል።

**4.10.3** ሕብረ-ብሔራዊ ሀገር የመፍጠር ትልምን እውን ለማድረግ ይረዳ ዘንድ የኢትዮጵያን ብዘሃነትን በሚገልፅ መልኩ ተጨማሪ የፌደራል መንግስት የሥራ ቋንቋዎች ስራ ላይ እንዲውሉ ይሰራል።

Addis Standard

## 4.11 ሀገራዊ ክብርን እና ሀገራዊ መቀራረብን የሚያመጣ የስፓርት ልማት

**4.11.1** ፓርቲያችን ሀገራችን ከአለም አቀፍ ውድድሮች ተገቢውን ደረጃና ውጤት እንድታገኝ እና በስፖርቱ መስክ የሀገራችን ክብር ከምንጊዜውም በላይ በዓለም መድረክ ከፍ እንዲል የሚያስችል ሁሉ-አቀፍ ስራዎችን ይተገብራል። ፓርቲያችን ስፓርትን የብሄራዊ ክብር ማሳያና ማስጠበቂያ ለማድረግ በሚያደርገው ጥረት በስፖርቱ ሀገራዊ ክብራችን የሚያጠለሹ ችግሮችን ለመፍታት እና ለመግታት ይሰራል።

**4.11.2** ፓርቲያችን ስፓርት ለሁሉም መርህን በሀገራችን ነባራዊ ሁኔታ እጅግ አስፈላጊ መሆኑን በመረዳት ሀገራዊ አንድነትና የህዝቦች ወንድማማችነትን ለማጠንከር ይሰራበታል።

**4.11.3** ፓርቲያችን ስፓርቱ ከመንግስት ጥገኝነት ማላቀቅና ህዝባዊነትን እንዲይዝ ማድረግ ወሳኝ መሆኑን በማመን ስፓርቱን ተቋማዊ እና በባለሙያው የሚመራ በማድረግ ህዝባዊ መሰረት እንዲይዝ ያደርጋል።

## 4.12 ህጋዊነትን በማረጋገጥ ህገ-ወጥ ስደት እና የሰዎች ዝውውርን መቆጣጠር

**4.12.1** ፓርቲያችን በህገወጥ ደላሎች የሚከናወን የውጭ ሀገር የስራ ስምሪት እንቅስቃሴ ላይ በህግ እና በተቋም የመከላከል ስራ በትኩረት ይሰራል። ይህንንም ለማድረግ የውጭ ስራ ፍለጋን ተከትሎ የሚስተዋለውን ህገ-ወጥ ስደትን ለመቀነስ፣ ህጋዊ በሆነ መንገድ ስራና ሰራተኛን የማገናኘት አሰራር እንደዘረጋ ያደርጋል።

**4.12.2** በውጭ ስራ የተሰማሩ ዜጎች ክብራቸው ተጠብቆና ለተገቢ አገልግሎት ተገቢ ክፍያ እንዲሰጣቸው ተገቢውን ክትትል እና ድርድር በማድረግ የዜጎች ደህንነት እና ክብር እንዲጠበቅ ይደረጋል።

## 4.13 የተፈጥሮና ሰው ሰራሽ ሀብቶችን ዘመንን እንዲሻገሩ የሚደርግ ጥበቃ

**4.13.1** ፓርቲያችን የኢትዮጵያዊ የጋራ እሴቶችና ወረቶች እንዲጠናከሩና እንዲጎለበቱ ይሰራል። የኢትጵያ የዘመን አቆጣጠር፣ ታሪካዊ ቅርሶች፣ ፊደላት አገሪቱ የሰው ዘር መገኛ መሆኗ፣ የጥቁር ህዝቦች ነጻነት መገለጫ መሆኗና እና መሰል ወረቶች ተገቢው ክብርና ትኩረት ተሰጥቷቸው ለሀገር ግንባታ መሳሪያ ሆነው እንዲያገለግሉ እና ለመጪው ትውልድ እንዲተላለፉ በትኩረት ይሰራል።

**4.13.2** የተፈጥሮ እና ሰውሰራሽ ሀብቶቻችን ከጊዜ ወደ ጊዜ የሚፈጠርባቸውን የመጥፋት አደጋ ለመካላከል የሚያስችል ስራዎች ተግባራዊ ይደረጋሉ። የመፈራረስ፣ የመጥፋት፣ የመበስበስና የመቃጠል አደጋ የተጋረጡባቸውን ታሪካዊ ቅርሶቻችን፣ ቁሳዊም ሆነ ቁስ ዘለል የሆኑ ባህላዊና ትውፊታዊ ቅርሶቻችንን ከጥፋት ለመታደግ አስፈላጊውን እንክብካቤ ያደርጋል።

Addis Standard

# ክፍል አምስት

## 5. የውጭ ግንኙነት ፕሮግራም

### 5.1 የውጭ ግንኙነት ዋና አላማ፡ ሀገራዊ ክብርን ማዕከል ያደረገ የውጭ ግንኙነት

ፓርቲያችን የውጭ ጉዳይን ከሀገር ውስጥ ጉዳይ የተነጠለ አድርጎ አይመለከትም። ይልቁንም የሀገር ውስጥ ጉዳያችን ፖለቲካዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ለውጦች ነፀብራቅ ሆኖ ዓለም አቀፍ ሁኔታዎችን ያልዘነጋ ነው። የውጭ ግንኙነታችንም የዲሞክራሲያዊት ኢትዮጵያ ግንባታን የሚያረጋግጥ፤ የሀገር አንድነትን በማስጠበቅ ብሔራዊ ክብርን የሚያስመልስ፤ ብሔራዊ ክብርን በማስመለስ ሀገራዊ አንድነትን የሚያጠናክር ይሆናል። ብሔራዊ ክብር የሌለው ሀገር ብሔራዊ ጥቅሙን ሊያስጠብቅ እንደማይችል ፓርቲያችን በጥብቅ ይገነዘባል። በመሆኑም የኢትዮጵያን ታሪክ እና አንድነት እንዲሁም የዜጎቿን ክብርና ተስፋዋን የሚያንፀባርቅ የጋራ ስምምነት ያለው ብሔራዊ ክብርን እና ብሔራዊ ጥቅማችንን የሚያስጠብቅ የተቀናጀና የተማከለ የውጭ ግንኙነት ፖሊሲና ትግበራን እውን ያደርጋል። ብሔራዊ ክብራችንን ለማረጋገጥ እና ጥቅሞቻችንን ለማስከበር፣ አስቀድሞ ግንኙነትን በማደስና በማጠናከር ላይ ያተኮሩ ሥራዎችን መሥራት ላይ ትኩረት በማድረግ በግንኙነት ብልሽት ምክንያት የምናጣቸውን ብሔራዊ ጥቅሞቻችንን ለማስከበር አመቺ ሁኔታ ይፈጥራል፡፡ በውጭ ግንኙነት መስክ ሀገራችን መልካም የሚባል ውጤት ያስመዘገበች ሀገር ብትሆንም የውጭ ግንኙነታችን ከጉድለት እና ከግድፈት የፀዳ አይደለም። ስለዚህ ግድፍቶቹን እና ጉድለቶችን መለየት፣ ማስተካከል እና መሙላት እንዲሁም የነበሩ ጠንካራ ጎኖችን ማስቀጠል የፓርቲያችን የውጭ ግንኙነት መሰረቶች ናቸው።

### 5.2 የውጭ ግንኙነት ግቦች

#### 5.2.1 ብሔራዊ ክብርን የሚያረጋግጥ የውጭ ግንኙነት

5.2.1.1 ፓርቲያችን የዜጎቻችን ክብር የብሄራዊ ክብራችን ዐይነተኛ መገለጫ እንደሆነ ይገነዘባል። በመሆኑም ዜጎቻችን በየትኛውም የዓለም ክፍል ቢሆኑ ክብራቸውን የሚያስከብር የውጭ ግንኙነት ስራ የፓርቲያችን የውጭ ግንኙነት መርሀ ግብር ቁልፍ መዳረሻ ነው፡፡ ፓርቲያችን የዜጎችን ክብር መሰረት ያደረገ ሀገራዊ ክብርን ለማስጠበቅ ዜጎችን መሰረት ያደረገና የዜጎችን መብት በየትኛውም የዓለም ክፍል ሊያስጠብቅ የሚችል የውጭ ግንኙነት ስራዎችን ይተገብራል።

5.2.1.2 ብዛት ያላቸው ኢትዮጵያውያን ወደ ተለያዩ የዓለም ክፍላት ስራ ፍለጋ ይሰደዳሉ። በሚልዮኖች የሚቆጠሩ ለስራ የወጡ ዜጎቻችንን ደህንነት፣ ክብር እና ኢኮኖሚያዊ ጥቅም ታሳቢ ያላደረገ የውጭ ግንኙነት የኢትዮጵያን ክብር ሊያስጠብቅ ስለማይችል ፓርቲያችን በውጭ ግንኙነት አነዚህን ዜጎቻችንን ታሳቢ ያደረገ ስራን ይሰራል። የሀገራችን ዜጎች ከውጭ የስራ ቅጥር የተሻለ ተጠቃሚ የሚሆኑበት እና መብቶቻቸውና ክብራቸው የሚጠበቅበት ሁኔታ ከቀጣሪ መንግስታት ጋር ስምምነትን በመፍጠር እንዲመቻች ያደረጋል።

5.2.1.3 የሀገራችንን መልካም ገጽታና የወደፊት ብሩህ ተስፋ ለውጭው ዓለም የሚያስተዋውቁ የውጭ ግንኙነት ሥራዎች ይሰራሉ።

Addis Standard

5.2.1.4 የፓን-አፍሪካኒዝም መሰረት የሆነችው ሀገራችን መላው ጥቁር ህዝቦች የሚያከብሩትና የሚያምኑትን ያህል ፓን-አፍሪካኒዝምን የሚያጠናክር የውጭ ግንኙነት ስራዎችን መተግበር ይኖርባታል። ፓርቲያችን ይህን በመረዳት የፓን-አፍሪካኒዝም መሰረትነታችንን የሚያጎሉ ስራዎች እንዲተገበሩ ያደርጋል።

### 5.2.2 ለትብብርና ለጋራ ተጠቃሚነት ትኩረት በመስጠት አጋሮቻችንን ማስፋት

5.2.2.1 ፓርቲያችን የተሻለው መንገድ በትብብርና ፉክክር መሃል ሚዛን መጠበቅ እንጅ ያልተገባ ፉክክር ተገቢ እንዳልሆነ በማመን የውጭ ግንኙነታችን ፖሊሲና ትግበራ ትብብርን፣ የጋራ ጥቅምን እና ሉአላዊነትን በማስከበር እና በማክበር ላይ የተመሰረተ መሆን እንዳለበት ያምናል፡፡ ችግሮችን ለመፍታትም ሆነ ብሔራዊ ጥቅምን ለማስከበር ቀዳሚው ነገር ግንኙነትን ማደስ እንደሆነ ያምናል። በመሆኑም በፉክክር እና በመቀናቀን ከሚመጣ አንጻራዊ ጥቅም ይልቅ ፍጹማዊ ጥቅምን የሚያስቀድም ውጭ ግንኙነት በመከተል አጋሮቻችን ለማስፋት ግንኙነትን ለማጠንከር አበክሮ ይሰራል፡፡

5.2.2.2 የምንኖርበት ዓለም ባለ ብዙ ዋልታ እንደመሆኑ ከየትኛውም ዋልታ ዲፕሎማሲያዊ ጥግ ሳንይዝ በዋልታዎች መካከል ዲፕሎማሲያዊ ሚዛንን በመጠበቅ ብሔራዊ ጥቅማችንን ለማስከበር ይሰራል። ዲፕሎማሲያዊ ሚዛንን በመጠበቅ ከነባር አጋሮች ጋር የነበረ ግንኙነት እንዲጠናከር ከመስራት ባሻገር ከአዳዲስ አጋሮች ጋር ዲፕሎማሲያዊ ግንኙነቶች ያደረጋል፡፡

### 5.2.3 የብዙዮሽ ትብብር ተቋማት ተሰሚነትን መጨመር እና ፖሊሲያዊ ነፃነትን ማስከበር

5.2.3.1 የብዙዮሽ ዲፕሎማሲን በመጠቀም አለም አቀፍ ተሰሚነታችንን ማሳደግ እና ከአለም አቀፍ ተቋማት ጋር ሉዐላዊነታችንን የጠበቀ መልካም ግንኙነትን መፍጠር ላይ ፓርቲያችን ይሰራል፡፡ የፖሊሲ ነፃነታችንንና ሉዐላዊነታችንን ባስጠበቀ መልኩ ከዓለም-አቀፍ ተቋማት ጋር የባለ ብዙዮሽ ትብብርን ለማጠናከር የሚያስችሉ ሥራዎች ይሰራል። ሀገራችን በብዙዮሽ ዲፕሎማሲ የአፍሪካ ድምጽ በመሆን የተባበሩት መንግስታት የፀጥታው ምክር ቤት ቋሚ አባል እንድትሆን ያላሰለሰ ጥረት ያደረጋል።

### 5.2.4 ለጎረቤት ሀገራት ትኩረት በመስጠት ዘርፈ ብዙ የጋራ ተጠቃሚነትን ማረጋገጥ

5.2.4.1 ሀገራችን ከጎረቤት ሀገራት ጋር በመተባበርና በጋራ ጥቅም ላይ የተመሰረተ ግንኙነት በመፍጠር አካባቢያዊ ሰላም እንዲረጋገጥ ፓርቲያችን በትኩረት ይሰራል። የአካባቢያዊ ሰላም ችግር የሆኑ ሽብርተኝነትና ሌሎችም የሰላም ጠንቅ የሆኑ ጉዳዮችን ለመግታት ከጎረቤት ሀገራት ጋር በመሆን በቅንጅት ይሰራል። በተጨማሪም ለአካባቢያዊ ሰላም መደፍረስ ምክንያት ሊሆኑ የሚችሉ በጎረቤት ሀገራት መካከል ያሉ መልካም ያልሆነ ግንኙነቶች እንዲሁም በጎረቤት ሀገራት ውስጥ ያሉ አለመግባባቶች ቀጠናዊ ችግሮችን ከመፍጠራቸው በፊት በሰላማዊ መልኩ መግባባት እንዲፈጠርባቸው የማግባባት ስራዎች ይሰራል፡፡

Addis Standard

5.2.4.2 በቀጠናው ካሉ ሀገሮች ጋር የጋራ ጥቅሞቻችንን መሠረት ያደረገ አካባቢያዊ የልማት፣ የኢኮኖሚ እና የሰላም ትሥሥር እንዲፈጠር በትብብር ይሰራል። ይህም ቀስበቀስ እያደገ የሚሄድ ቀጠናዊ የኢኮኖሚ ትስስር እንዲሆን አስፈላጊውን ጥረት ያደርጋል። ይህንንም ለማድረግ በቀጠናችን ያሉ ነባር አካባቢያዊ ድርጅቶች እንዲጠናከሩ ለማድረግ እንዲሁም ድርጅቶቹ ለቀጠናዊ ትስስር መፈጠር መሰረት እንዲጥሉ በትኩረት ይሰራል፡፡ በተጨማሪም እነዚህ አካባቢያዊ ድርጅቶች የቀጠናው የተበታተኑ ድምፆች ወደ አንድ መሰባሰቢያ በማድረግ የቀጣናው ሀገራት የመደራደሪያ አቅም እንዲሆኑ ጥረት ያደርጋል፡፡

5.2.4.3 ከጎረቤቶቻችን ጋር በሚያገናኙን የተፈጥሮ ሃብቶች ላይ በጋራና ፍትሃዊ ተጠቃሚነት መርህ የሃገራችንን ጥቅም ለማስከበር ፓርቲው ይሰራል። ድንበር ተሻጋሪ ወንዞቻችንን የመጠቀም መብታችንን ባከበረ፣ ዓለም-አቀፍ የድንበር ተሻገሪ ወንዞች መርሆዎችን በተንተራሰ መልኩ ለጥቅም እንዲውሉ ደረጋል። እንዲሁም በአጠቃቀም ምክንያት የሚመጡ አለመግባባቶችም በዓለም-አቀፍ መርሆዎችና በዲፐሎማሲያዊ መንገዶች እንዲፈቱ በዘላቂነትም በወንዞቹ ላይ ሁሉን አቀፍ የሆነ ስምምነት እንዲደረስ ያደረጋል። በተመሳሳይ ሀገራችን በአካባቢያችን ካሉ ባለ ወደብ አገሮች የተሻለ የወደብ ተጠቃሚነት መብት በሚያረጋግጥ መልኩ አካባቢያዊ ትብብሮች ላይ ትኩረት በመስጠት እንዲሰራ ያደረጋል።

## 5.2.5 የኢትዮጵያውያንና ትውልደ-ኢትዮጵያውያን ተሳትፎ ማሳደግ

5.2.5.1 ከሀገራቸው ጋር የተለየ ቁርኝት ያላቸው በውጪ የሚኖሩ ኢትዮጵያውያን እና ትውልደ-ኢትዮጵያውያን ከሀገራቸው ፖለቲካዊ፣ ኢኮኖሚያዊ እና ማኅበራዊ ሁኔታዎች የተነጠሉ እንዳይሆኑና ተጠቃሚ እንዲሆኑ ሁኔታዎችን ያመቻቻል። በዚህ ጉዳይ ኤምባሲዎቻችን ከምንም ጊዜ በላይ በውጪ ላሉ ዜጎች እና ትውልደ-ኢትዮጵያውያን ክፍትና ቅርብ ይሆናሉ። ለመብቶቻቸው ቀድሞ ደራሽና ጠበቃ፣ ለደህንነታቸው ቀዳሚ ዋስትና እንዲሆኑ ያደረጋል።

5.2.5.2 በውጭ የሚኖሩ ኢትዮጵያንና ትውልደ- ኢትዮጵያውያን በሀገራቸው ጉዳይ ላይ ባለቤት እንዲሆኑ ከሚደረገው ጥረት ባሻገር በየሚኖሩበት ሀገር የኢትዮጵያ አምባሳደሮች እንዲሆኑ ማበረታታት ላይ በትኩረት ይሰራል።

## 5.2.6 ብሔራዊ ክብርን እና ብሔራዊ ጥቅምን የሚያስጠብቅ የውጭ ግንኙነት የመፈፀም አቅም መገንባት

5.2.6.1 ፓርቲያችን የኢትዮጵያን ታሪክ እና አንድነት አንዲሁም የዜጎቿን ክብር እና ተስፋዋን የሚያንፀባርቅ የጋራ ስምምነት ያለው ብሔራዊ ክብራችንን እና ብሔራዊ ጥቅማችንን የሚያስጠብቅ የተቃናጀ እና የተማከለ የውጭ ግንኙነት ፖሊሲና ትግበራ እውን ይደረጋል፡፡ የውጭ ግንኙነት ተቋሞቻችን ውጭ ግንኙነትን የማስፈጸም አቅማቸው የላቀ እንዲሆን የመምራት አቅም ባላቸው አመራሮችና የመፈጸም ብቃት ባላቸው ባለሞያዎች እንዲዋቀሩ ያደረጋል። አምባሳደሮቻችን የሀገራችንን ስምና ክብር እና የኢትዮጵያን አንድነት የሚያንጸባርቁ መሆናቸውን ፓርቲያችን ያምናል፡፡ በመሆኑም

Addis Standard

አምባሳደሮች ሀገራችንን እና ታሪኳን ጠንቅቀው የሚያውቁ እና ብሔራዊ ክበራችንን የሚያስጠብቁ ከፍተኛ የዲፕሎማሲ እውቀት ያላቸው እንዲሆኑ ይደረጋል፡፡ በተጨማሪም የውጭ ግንኙነት ዘርፉና ተቋማት ወቅቱን ባገናዘበ ሀገራዊ ሁኔታዎች እና አለምአቀፍ እድገቶች በተቃኘ መልኩ እንዲያድጉ እና እየተለወጡ እንዲመጡ ይሰራል፡፡

5.2.6.2 የውጭ ግንኙነት ማስፈጸሚያ ብሔራዊ አቅማችን በአገር ሃይል አቅማችን ላይ እንዲመሰረት ሰፊ ጥረት ያደረጋል። ይህም ካለን ወረት በተጨማሪ በቀጣይ በሚከናወኑ የመልካም ገጽታና አዎንታዊ ተጽዕኖ መፍጠሪያ ተግባራት በመነሳት እየተገነባ የሚሄድና በጎረቤቶቻችንም ሆነ ሌሎች ሃገራት ጋር በምንፈጥረው መተማመን ላይ የተመሰረተ ግንኙነት እየዳበረ የሚሄድ ይሆናል። ለዚህም የህዝብ ለህዝብ ግንኙነትና ዲፕሎማሲ ላይ ትኩረት ተሰጥቶ ይሰራል።

5.2.6.3 የሀገራዊ ሉዓላዊነት ማስጠበቅ ጉዳይ በአገር ኃይሎች አቅም ብቻ የሚመለስ ባለመሆኑ ሃገራዊ ክብራችንን ሳይደፈር የመግታት አቅም ያለው ጠንካራ፣ ዘመናዊና ሁሉን-አቀፍ ወታደራዊ ኃይል መገንባት ይገባል ብሎ ፓርቲያችን ያምናል። በመሆኑም የመከላከያ አቅማችን የዘመኑን ዐውደ-ውጊያ የዋጀ፣ በዋናነት ጥቃትን ከወዲሁ የማስቀርት አቅምን መሠረት የሚያደርግ፣ በማንኛውም መስክ (በምድር፣ በአየር፣ በሳይበር እና በባህር) የሚቃጡትን ትንኮሳዎችን መመከት የሚችል፣ ለዜጎቻችን ኩራት በሚሆንና ብሔራዊ ጥቅማችንን በሚያስጠብቅ መልኩ እንዲደራጅ ያደርጋል።

5.2.6.4 ብሔራዊ ክብራችንን እና ብሔራዊ ጥቅማችንን ሊያስከብር የሚችል ዘርፈ-ብዙ ዲፕሎማሲን የመተግበር አቅማችንን ማሳደግ እና መተግበር ላይ ትኩረት ያደርጋል፡፡ ሁሉን አቀፍ ዲፕሎማሲን በመተግበር የትብብር ዘርፎችን ማስፋት ፓርቲያችን ቅድሚያ ሰጥቶ ይሰራል፡፡ በዚህም የሰላም፣ የኢኮኖሚ፣ ዜጋ-ተኮር እና ፐብሊክ ዲፕሎማሲ የውጭ ጉዳይ ፖሊሲ ዋነኛ መተግበሪያ ስትራቴጂ ሆነው እንዲሰራባቸው ትኩረት ይሰጣል። በሌላ በኩልም ለመገንባት ለምንጥረው አውቀት መር ኢኮኖሚ እና በሳይንስና ቴክኖሎጂ የሚፈለገው የእድገት ደረጃ ላይ ለመድረስና ከቀደሙት ሀገራት ልምድን ለመቅሰምና እውቀት ሽግግር ለማድረግ የሳይንስ ዲፕሎማሲን የሚያጠናክሩ ሥራዎች ይሰራል።

Addis Standard